**የኢትዮጵያ የለውጥ ሂደት፣ የቀጣዩ ምርጫ አገራዊ ፋይዳ እና የተደቀኑ አደጋዎች**

**ከኢዜማ መሪ ለኢትዮጵያ ህዝብ የተላለፈ መልዕክት**

# የኢትዮጵያ የለውጥ ሂደት፣ የቀጣዩ ምርጫ አገራዊ ፋይዳ እና የተደቀኑ አደጋዎች

# ከኢዜማ መሪ ለኢትዮጵያ ህዝብ የተላለፈ መልዕክት

## ውድ ኢትዮጵያውያን ወገኖቼ፤ እንደምን ከረማችሁ

በዛሬው ዕለት እንደ ኢዜማ መሪም ሆነ እንደ አንድ ዜጋ፣ ከኢትዮጵያውያን ወገኖቼ ጋር በዚህ መልክ ለመገናኘት ምክንያት የሆነኝ ከፊታችን በተደቀነው ምርጫ ላይ ኢዜማን እንድትመርጡ ለመቀስቀስ አይደለም። እሱ ሁሉም የፖለቲካ ድርጅቶች የምርጫው ቅስቀሳ ጊዜ በግልጽ ሲታወጅ የምናደርገው ይሆናል። ይልቁንም ዛሬ ላዋያችሁ የምፈልገው እንደ አገርም እንደ ህዝብም ልንጋፈጠው የሚገባን ፊት ለፊታችን የተጋረጠ አንድ ትልቅ እውነትን ነው፤ . . . ዛሬ በተለያዩ የአገራችን አካባቢዎች የሚከሰቱ አለመረጋጋቶች፣ ግጭቶችና ከዕለት ወደ ዕለት አሳሳቢ እየሆነ የመጣው የሰላም ዕጦት፣ ነገ ደግሞ ምን ይዞ ይመጣ ይሆን የሚል ስጋት/ጭንቀት አለ።

በየሚዲያው የሚወጡ፤ የተጨበጡና ያልተጨበጡ ሁላችንንም የሚያስጨንቁ በርካታ መረጃዎችን እንሰማለን። ተማሪዎች ታገቱ/ተገድሉ፥ መስጊድና ቤተ-ክርስቲያን ተቃጠሉ፥ ባንኮች ተዘረፉ፥ መንገድ ተዘጋ፥ ንብረት ተዘረፈ ወይም ወደመ፣ የሚሉ ዜናዎችን መስማት ከምንግዜውም በላይ እየተለመደ ነው። ከመደበኛ ስራችን ውጭ በተለያዩ ማህበራዊ ስብስቦች ስንገኝ የምንወያያቸው ጉዳዮች **ለመሆኑ አገራችን ወዴት እየሄደች ነው?** በዚህ በምናየውና በምንሰማው ሁኔታ ከቀጠልን **እንደ አገር መቀጠል እንችላለን ወይ?** ከዚህ ከገባንበት አዘቅት መቼና እንዴትስ ነው የምንወጣው? የኛም ሆነ የልጆቻችን ዕጣ ፈንታስ ምን ይሆናል? የሚሉና ሌሎችም ብዙ ይህ ትውልድ ወደደም ጠላ መመለስ ያለባችው አንኳር አገራዊ ጥያቄዎች፤ አዋቂና ህጻን ሳይለይ ሁላችንንም ከምንም በላይ ያስጨነቁና እንቅልፍ እየነሱ የሚገኙ ጥያቄዎች ሆነዋል።

ዛሬ አገራችን ወሳኝ የታሪክ ምዕራፍ ላይ ቆማለች፥ በዚህ ወሳኝ የታሪክ ምዕራፍ ላይ የሀገራችን የወደፊት እጣ ፈንታ ሲወሰን ውሳኔዉ እያንዳንዱን ኢትዮጵያዊ ይመለከታልና በዚህ ትልቅና ታሪካዊ ውሳኔ ላይ እኛ ምን ያገባናል? ምንስ ሚና አለን? ለአገራችን ይበጃል የምንለውና የምንፈልገው የመልካም ዘመን መዳረሻ ጋር እንድንደርስ ምን ማድረግ አለብን?" ለሚሉ ጥያቄዎች መልስ ማቅረብ የእያንዳንዱን ኢትዮጵያዊ የነቃ ተሳትፎ የሚጠይቁ ነገር ግን ዛሬ ላይ ሁላችንንም ግራ ያጋቡ ጥያቄዎች ናቸው።

ከፊታችን ያለውን ምርጫ እንኳን በሚመለከት የምናደርገው ውይይት በምርጫው ማን ያሸንፋል? ወይንም ማን ቢያሸንፍ ጥሩ ነው? የሚል ክርክር ሳይሆን **"ለመሆኑ በዚህ አይነት አገራዊ ሁኔታ ነፃና ሚዛናዊ ምርጫ ማድረግስ ይቻላል ወይ?" "ቢቻልስ አገራችን ውስጥ የሚታዩት ዘርፈ-ብዙና ዉስብስብ ችግሮች አገራዊ ምርጫ በማድረግ የሚፈቱ ናቸው ወይ?** የሚሉ የጊዜው ሁኔታ የፈጠራቸው ፍርሀቶችና ጭንቀቶች ላይ ደርሰናል። ይህ ሁሉ የሚያሳየን ሁሉም የፖለቲካ ኃይሎች ጊዜያዊ ከሆነ የራሳችንን ጥቅምና ፍላጎት ለጊዜውም ቢሆን ተወት አድርገን በጋራ ልንሰራባቸው የሚገቡ የአገራችንን ትላልቅ ችግሮች በጋራ ለመፍታት አንድ ላይ ካልቆምን የአገራችን የኢትዮጵያ ህልውና ከምን ጊዜውም በላይ አሳሳቢ ሁኔታ ላይ ይወድቃል።

የአገራችንን ሁኔታ በተመለከተ ከተለያዩ የዜና ምንጮች ከምንሰማው በተጨማሪ፣ ኢዜማ አገራዊ ፓርቲ ሆኖ ከተፈጠረ በሁዋላም ሆነ ከዚያ በፊት፣ በገጠርና በከተማ፣ በተለያዩ አካባቢዎች ከሚገኙ የተለያዩ የህብረተሰብ ክፍሎች ጋር የአገራችንን ሁኔታ በተመለከተ ሰፊ ውይይቶች አድርገናል። አሁንም በሁሉም የአገሪቱ አካባቢዎች በዘረጋነው የፓርቲያችን መዋቅር አማካኝነት አካባቢያዊ መረጃዎችን ስለምንሰበስብ ስለ አገራችን ሁኔታ፥ ፊት ለፊታችን ስለተጋረጡት ችግሮች፣ በህዝቡ ውስጥ ስለሚንፀባረቁ ጭንቀቶች፣ ስጋቶችና ተስፋዎች በቂ መረጃ አለን ብለን እናምናለን።

ኢዜማ በአንድ በኩል እንደ አንድ ኃላፊነት የሚሰማው አገር አቀፍ የፖለቲካ ድርጅት ኢትዮጵያ ውስጥ የሚከሰቱ የተለያዩ ችግሮችን እያየ ከንፈር በመምጠጥ፥ በማዘንና በመተከዝ አያልፍም። በሌላ በኩል ደግሞ ኃላፊነት በጎደለው መንገድ የህዝቡን ስሜት አነሳስቶ ችግሮችን የበለጠ አያጦዝም። ድርጅታዊ አቅማችን እስከፈቀደ ድረስ ፊታችን ላይ የተደቀኑ አደጋዎችን በመረጃ ላይ ተመርኩዘን በመተንተን አደጋዎቹ ከቁጥጥር ውጭ ወጥተው የአገራችንን ህልውና አደጋ ላይ ከመጣላቸው በፊት ለማህበረሰባችን የማንቂያ ደውል እናሰማለን። አደጋዎቹን መከላከልና ብሎም ማቆም የሚያስችል ስትራቴጂ እንቀይሳለን። ከተለያዩ የአገራችን ባለድርሻዎች፥ የፖለቲካ ድርጅቶች፣ የሲቪክ ማህበራት፣ ምሁራንና ከመንግስት አካላት ጋር በመሆን፣ በአገራችን የተደቀኑትን አደጋዎች በጋራ መመከት እንዲቻል የማስተባበር ሥራ እንሰራለን። ከሁሉም በላይ ደግም በፖለቲካ ድርጅቶች መካከል ያለው የፖሊሲና የፖለቲካ አመለካከት ልዩነቶች እንደተጠበቁ ሆነው፣ አሁን የምናያቸውን አገራዊ አደጋዎች መከላከል ብቻ ሳይሆን እንደገና እንዳይከሰቱም ለማድረግ "የብሔራዊ ጥቅሞቻችንና የአገር አጠቃላይ ደህንነት ጉዳዮች " (National Interest & Securtiy Aagendas) ናቸው በሚባሉ ጉዳዮች ላይ ከሁሉም ባለድርሻ አካላት ጋር አብሮ ለመስራት ባለን ድርጅታዊ አቅም ሁሉ እንዘጋጃለን።

ዛሬ በዚህ ንግግር ላይ የማተኩረው ኢዜማ እንደ ድርጅት በአገራችን ያለውን ሁኔታ ገምግሞ የደረሰባቸውን ከፊታችን የሚታዩ አደጋዎች ምንነት፤ እነኝህን አደጋዎች በሚመለከት የጋራ ሀገራዊ ግንዛቤ ለመፍጠር የሚያስችል የሰከነ ውይይት ለመከፈትና፤ እኛ የሚታየን አደጋ በርግጥም ሌሎቹም የአገራችን ባለድርሻዎች ይታያቸው ከሆነ፣ ይህን አደጋ ለመከላከል የሚያስፈልገውን የጋራ ስምምነትና እንቅስቃሴ ለማድረግ የሚያስፈልገውን አገራዊ ጥሪ ለማስተላለፍ ነው።

እኛ ባደረግነው የአገራዊ አደጋ ትንተና የማይስማሙ ኃይሎች ሊኖሩ እንደሚችሉ እንገነዘባለን። እነሱም ቢሆኑ ግን ዝም ብሎ የተለመደውን ጭፍን ወገንተኛ የሆነ፤ በቅጡ ያልታሰበበት የጥቅል ተቃውሞ ከማሰማት ይልቅ "በርግጥ ይህ አደጋ አለ ወይ?" ብለው በጥሞና እንዲያስቡ ካደረጋቸውና ወደ ሰከነ ውይይት ከመራቸው፣ የዚህ መልዕክት ዓላማ በከፊልም ቢሆን ተሳክቷልና ለምን ከእኛ ትንተናና ድምዳሜ ጋር ሙሉ ለሙሉ አልተስማማችሁም አንልም።

## ለለውጡ ምክንያት የሆኑት ዋና ዋና ጉዳዮችና ችግሮች ምንድን ነበሩ?

አገራችን ኢትዮጵያ እንደ አገር በቆየችባችው ረዥም አመታት ውስጥ እንደዛሬዎቹ ታላላቅ የአውሮፓ አገሮች በተለያዩ የአገረ መንግስት ግንባታ ሂደቶች ውስጥ አልፋለች። ሆኖም የአውሮፓ አገሮች የአገረ-መንግስት ግንባታ ሂደታቸውን አጠናቀው ዛሬ ለደረሱበት ከፍተኛ የእድገትና ሥልጣኔ ደረጃ ሲበቁ አገራችን ለዚህ ሳትታደል ዛሬ ላይ ደርሳለች። በዚህ የረጅም ጊዜ የታሪክ ሂደት በየጊዜው በሥልጣን ላይ የመጡ መንግስታት አገሪቱን ለማዘመን የሞከሩትን ያህል፤ ልክ እንደ አውሮፓ መንግስታዊ ሥርዓቶች፤ ብዙ የመብት ጥሰቶችንና በደሎችን በሕዝባቸው ላይ ፈጽመዋል። እነኝህን በደሎችና የፍትህ

ማጣቶች ለመታደግ እንደ አውሮፓ አገሮች ባይሳካልንም ባለፉት አንድ መቶ አመታት ጊዜ ውስጥ ፍትሃዊ መንግሥትዊ ሥርዓት ለመመስረት በተለያዩ ቦታዎች ማህበራዊ እንቅስቃሴዎች (የገበሬዎች እንቅስቃሴዎች) አድርገናል። በተለይ ባለፉት 50 አመታት አገራችንን ከገባችበት የኋላቀርነት ቅርቃር ለማውጣትና ለማዘመን፤ ለሁላችንም የቆመ የጋራ መንግሥት እንዲመሰረት ለማድረግ ጠንካራ የሚባሉ ሕዝባዊ እንቅስቃሴዎች ተደርገዋል። እነኝህ የሕዝብ እንቅስቃሴዎች በጊዜው ያሉትን መንግሥታት እስከመጣል ደርሰው በ66ቱ አብዮት የአጼዎችን የመንግሥት ሥርዓት ለማስወገድ ቢቻልም፣ በምትኩ በሕዝብ የተመረጠ መንግሥት መመስረት አቅቶን እንዲያውም እልም ያለ አምባገነናዊ ሥርዓት ተፈጥሮ የብዙ ወጣቶችንና ምሁራን ህይወት ገብረናል፤ የአገራችንን ኢኮኖሚም አሽመድምደናል።

ይህንን የአምባገነን ሥርዓት ለመጣል በተደረገ ትግልም ወደፊት የሚያይ፣ የተገራና ሁሉንም ኢትዮጵያውያን በእኩል አይን የሚያይ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓተ-መንግስት መፍጠር ተስኖን፤ ማህበረሰብን በጠባብ የዘውግ መለኪያ ብቻ የሚመለከት የአድሎ ሥርዓት ፈጥረን ሰላምና መርረጋጋት ማምጣት ሳንችል ቀርተናል፡፡ በተጨማሪም ሁሉንም የህብረተሰብ ክፍል በተገቢው ደረጃ ተጠቃሚ የሚያደርግና ከከፋ ድህነትና አልእኩልነት (Inequality) የሚያላቅቅ ፈጣን ልማት ማረጋገጥ ባለመቻላችን፣ በታሪካችን ለሶስተኛ ጊዜ ትልቅ የለውጥ ሂደት ውስጥ ገብተን ደፋ ቀናውን ተያይዘነዋል።

ይህ ዛሬ የተያያዝነው የለውጥ ሂደት ወደምንፈልገው የተረጋጋ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ይውሰደን አይውሰደን ገና የታወቀ ነገር የለም። ነገር ግን ከላይ በመግቢያዬ ላይ እንደጠቀስኩት አሁን በማህበረሰባችን ውስጥ እየተብላሉ ያሉትን ጭንቀቶችና ስጋቶች ስንመለከት ይህ ያሁኑ የለውጥ ሂደት ያለፈው ለውጥ ይዟቸው በመጣቸው ብዙ ህፀፆች ምክንያት፤ ባንድ በኩል ሌላው የሰው ልጅ በስልጣኔ ሂደቱ ለሰላማዊ ኑሮ፥ ለተረጋጋ የፖለቲካ ስርዓትና ለሁለንተናዊ እድገት አይበጁም ብሎ ወደተዋቸው ትናንሽ የዘውግ መንግሥታት ፈጠራና ከዚሁ ጋር ተያይዞ ወደሚመጣው ማለቂያ የሌለው የዕርስ በርስ ጦርነት ለመግባት የቸኮልን ይመስላል። በሌላ በኩል ደግሞ ወደፊት ተመልክተን ጠንካራ አገራዊ፣ ለህገመንግስት የሚገዛና ማህበረሰቡን የሚያከብር መንግሥት ፈጥረን ወደ ስልጣኔ እርከን እንኄድ ይሆን በሚለው መንታ መንገድ ላይ የቆምን ይመስላል። ከነኝህ ሁለት አማራጮች የትኛውን መንገድ እንመርጣለን? የሚለውን ለመመለስ ግን ባጭሩም ቢሆን ይህ ያሁኑ የለውጥ ሂደት እንዲመጣ ግፊት ያደረጉትን ሁኔታዎች ማየቱ ይጠቅማል።

በህወሓት የሚመራውና በስተመጨረሻው የሌሎችንም የብሄር ድርጅቶች አሰባስቦ የደርግን መንግሥት ለመጣል የተሳካ ትግል ያደረገው ኃይል ሁለት ተቃራኒ ሊባሉ የሚችሉ አመለካከቶችን (ባንድ በኩል ወደፊት የሚያይ የሶሻሊስት ርዕዮተ ዓለም በሌላ በኩል ደግሞ ወደኋላ የሚያይ የዘውግ ፖለቲካ) አያይዞ ባደረገው ትግል ላይ የተቀየረው የዓለማችን ሁኔታ ረድቶት ወደ ስልጣን ሲመጣ እነኝህን ሁለት አመለካከቶች ባንድ ላይ ይዞ መጓዝ የተቀየረው የአለም ሁኔታ (የሶቭየት ህብረት መፈራረስና ይዞ የሚጓዘው የኮሙኒስት ርዕዮተ ዓለም መክሰም፤ የካፒታሊዝም ሥርዓት ብቸኛው አማራጭ መሆን) አልፈቀደለትም። ስለዚህም የሶሻሊስት ርዕዮቱን ጥሎ፤ ግን ደግሞ አገሪቱን ለመግዛት ያስፈልገኛል ያለውን የዘውጌ ፖለቲካ አጥብቆ ይዞ ነበር የመንግሥት ሥርዓቱን ያስጀመረው። በስልጣን ለመቆየት በሚል የተገራ የመንግሥት ስርዓት አቆማለሁ ብሎ የጀመረው የዴሞክራሲያዊነት ጭምብል በስልጣን እንደማያቆየው ሲያውቅ በ"እድገት መንግሥትነት" ስም ኢኮኖሚውን ለዘውጌ ልሂቃን መጠቀሚያ በሚሆን የተደራጀ የሙስና ቀለበት ውስጥ አስገብቶ ራቁቱን የወጣ የዝርፊያ ሥርዓት ማካሄድ ጀመረ። በዚህም ብዙ አዳዲስ ከመንግሥት ሥርዓቱ ጋር የተነካኩ በወዝና ላባቸው ያልከበሩ ባለሀብቶችን ፈጠረ። ሆኖም ይህ የዘውግ

ፖለቲካ አካሄድ በመሰረታዊ መልኩ የአድሎ አካሄድ በመሆኑ የኃብት ማካበቱ ሂደት ከፍተኛውን የስልጣን እርከን ወደተቆጣጠረው ዘውጌ ድርጅት ማዘንበሉ አልቀረም። ይህ ደግሞ ከዋናው የዘውግ ድርጅት በታች በመሆን ክልሎችን በሚቆጣጠሩት የዘውግ ድርጅቶች ውስጥ ቀስ እያለ እየደነደነ የሄደ የቅሬታና አልፎም የበቀል ስሜትን በህዝቡ ዘንድ እየፈጠረ ሄደ።

በሌላ በኩል ደግሞ የለውጡ ሂደት ከአምባገነናዊ ሥርዓት ቀስ እያለ ወደ ተገራ የመንግሥት ሥርዓት ይሄዳል ብሎ በተለይ በመጀመሪያው ጊዜ የነበሩ ዴሞክራሲያዊ የሚመስሉ አካሄዶች ላይ ተስፋ አድርጎ የተንቀሳቀሰው የማህበረሰብ ክፍል፣ እያደር ሥርዓቱ በሥልጣን ለመቆየት በሚወስዳቸው አምባገነናዊ አካሄዶችና ይልቁንም በመንግሥት ግፊት በማሕበረሰቡ ውስጥ እየተጠናከረ የሄደው ዘውጌያዊ ክፍፍልና መናቆር ያስፈራው አካል የመንግሥቱን አካሄድ መኮነንና አንዳንዴም መገዳደር ጀመረ።

ከዚህ በተጨማሪ ሥርዓቱ የተመሰረተበት የዘውጌ ፌደራሊዝም ቃል የገባውን እውነተኛ ፌደራላዊ ስርዓት ተግባራዊ ለማድረግ የማይችል መሆኑ የታያቸው ከመንግሥት ውጭ ያሉትም የዘውጌ ድርጅቶች ይህንን የመንግሥት ሥርዓት በተቀናበረ ሁኔታ፤ በመንግሥት ውስጥ ካሉና የሚካሄደው የአድሎ አካሄድ ካስመረራቸው የዘውጌ ፖለቲከኞች በሚያገኙት ድጋፍ በመበረታታት ፀረ-መንግሥት እንቅስቃሴያቸውን አፋፋሙት። ይህ በተለያዩ ኃይሎች፤ አንዳንዴ በተናጠል ሌላ ጊዜ ደግሞ በመተባበር የተደረገ ትግል ያለውን መንግሥት በነበረበት ሁኔታ ማስቀጠል እማይቻልበት ደረጃ ላይ ሲደርስ ሥርዓቱ መፈረካከስ ጀመረ።

በራሱ ሥርዓት ውስጥ ያሉና የመንግሥት አካሄድ ያልተስማማቸው ኃይሎች የለውጥ መምጣትን ግዴታነት በማየት ባደረጉት የውስጥ ትግል ሥርዓቱን ሙሉ ለሙሉ ከማፍረስ ይልቅ ቀስ በቀስ በሚሄድ ዘገምተኛ የለውጥ ሂደት፤ በተለያዩ የውስጥ ግፊቶች የተፈጠረውን የማህበረሰቡን የለውጥ ፍላጎት አቻችለን የአገሪቱን አንድነት ባስጠበቀ፤ ግን ደግሞ ዘውጌ ማህበረሰባት ያላቸውን የራስን በራስ የማስተዳደር ፍላጎት በእውነተኛ ፌደራላዊና ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት አጣጥመን አገሪቱን ወደ ቀጣዩ የስልጣኔ ሂደት እንወስዳለን በሚል የተስፋ ቃል ነበር የለውጡ ሂደት የተጀመረው። በዚህ የተስፋ ቃልም በመተማመን ያለውን መንግሥት በተለያየ መንገድ ለመጣል ይታገሉ የነበሩ በአገር ውስጥም ሆነ በውጭ አገሮች የነበሩ ኃይሎች የሚከተሉትን የፖለቲካ መስመር በሕጋዊና በሰላማዊ መንገድ እንዲሁም የሕዝቡን ፍላጎት በሚያንጸባርቅ እውነተኛና ሰላማዊ የምርጫ ሂደት ለመገዛት ተስማምተው ከያሉበት ወደ አገር የገቡትና የለውጡን ሂደት የተቀላቀሉት።

ይህ የለውጥ ሂደት ሲጀመር ከዚህ በፊት እንደነበሩት የለውጥ ሂደቶች ማህበረሰቡን በማያተራምስ መንገድ፤ ባለፈው ላይ የነበረውን ቅሬታና ቁርሾ አስወግዶ ወደ ፊት በመመልከት የሚካሄድ መሆኑ በጣም አብዛኛውን የአገራችንን ህዝብ ያስደሰተ እንደነበር ሁላችንም እናስታውሳለን። ያም ሆኖ ግን እነኝህ የተለያየ አላማ ይዘው ለለውጥ ይንቀሳቀሱ የነበሩ ኃይሎችም ሆነ ለግል ጥቅማቸው ሲሉ ለውጡን እንደግፋለን ብለው ከለውጥ ኃይሉ ጋር ለጊዜው የተሰለፉ በመንግሥት ውስጥ በተለያየ የሥልጣን እርከንና በየክልሉ የነበሩ ኃይሎች ለውጡን ለማደናቀፍም ሆነ በለውጡ የሚፈልጉትን አላማ ለማሳካት በለውጡ ጅማሮ ከተቀመጠው የአካሄድ ሕግ ውጭ መንቀሳቀስ የጀመሩት ብዙም ሳይቆዩ ነበር።

ለውጡ የተጀመረው ከለውጡ በፊት የነበረውን መዋቅር ሙሉ ለሙሉ በማፈራረስ ሳይሆን ቀስ በቀስ የነበሩ ህፀፆችን እየነቀሰ ባለው መልካም ሁኔታ ላይ እየጨመረ ለመሄድ ስለነበረ፣ ቀድሞ ለነበረው ያገዛዝ ስርዓት አስፈላጊ የነበሩ፤ በተለይ በየክልሉ

ላሉ የዘውጌ ድርጅቶች ተጠሪ የሆኑ ወታደራዊም ሆነ አስተዳደራዊ ኃይሎች ከተቀመጠው የለውጥ ሂደት አካሄድ ውጭ የሚንቀሳቀሱ የዘውጌ ኃይሎችን ከመቆጣጠር ይልቅ እያዩ እንዳላዩ በመሆን፣ አንዳንዴም ከነኝህ ኃይሎች ጋር በማበር ቀስ በቀስ በማዕከላዊ መንግሥት ስልጣን ላይ ያለውን ኃይል ማዳከሙን ተያያዙት። አገራዊ ለውጡን የሚመራው ኃይል ተዳክሟል ብለው ባመኑበትና ማዕከላዊው መንግሥት ሰላም የማስጠበቅ አቅም ከመገንባቱ በፊት ማህበረሰቡ በለውጡና በለውጡ ኃይሎች ተስፋ እንዲቆርጥ በየቦታው በሚቀሰቅሷቸው ባመዛኙ ከዘውግ ጋርና አንዳንዴም ከሃይማኖት ጋር በተያያዙ ግጭቶች የሚሞተውና ከቀዬው በሚፈናቀለው የሕዝብ ብዛት ምክንያት ማህበረሰቡ **"በርግጥም መንግሥት የለም"** ብሎ ተስፋ እንዲቆርጥ፤ ሥርዓት አልበኝነት በአገሪቱ እየነገሰ ነው ብሎ እንዲሰጋና ለደህንነቱ ሲል ሁሉም ወደየዘውጌ ምሽጉ እንዲገባ ወይንም ታግሎ የጣለውን አምባገነናዊ ስርዓት እንዲናፍቅ ለማድረግ ያላሰለሰ ጥረት ማድረጉን ቀጠሉበት።

ይህን እንቅስቃሴ ሶስት ዓይነት ኃይሎች በማወቅም ሆነ ባለማወቅ በመደጋገፍ ሲያካሂዱት ቆይተዋል። የመጀመሪያውና ምናልባትም ዋናውን ሚና የሚጫወቱት ይህ ለውጥ በርግጥም ወደ ተረጋጋ ዴሞክራሲያዊ ስርዓት ከሄደ እስካሁን በስልጣን ላይ በመሆን ያገኘነውን ጥቅም እናጣለን ብለው የሚሰጉ የቀድሞው ሥርዓት ዋነኛ ተጠቃሚዎች ናቸው። እነኝህ ኃይሎች ከህዝብ የተዘረፈ ከፍተኛ ገንዘብ አላቸው። ከዚያም በላይ ግን ከቀድሞው ሥርዓት ጋር ተያይዘው የመጡና እስካሁንም ያልፈረሱ ትላልቅ ለየክልሉ ዘውግ ታዛዥ የሆኑ ወታደራዊና አካባቢ መንግሥት አስተዳደራዊ አቅም፤ እንዲሁም የሚዲያ ተቋማት አሏቸው።

ሁለተኛው ኃይል ለውጡን የሚፈልግ ኃይል ነው፥ ሆኖም ይህ ኃይል የሚፈልገው መንግሥትን ለመግራትና አገራዊ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓትን ለመመስረት አይደለም። የቀድሞውን ዘውጌያዊ ሥርዓት በበላይነት ይመራ የነበረውን የዘውግ ቡድን ከተሰቀለበት ማማ አውርዶ፤ አሁን በባለተራነት የየዘውጌ ክልሉን እንደፈለግን እንገዛለን፤ ማዕከላዊ መንግሥቱን አዳክመን ከሞላ ጎደል በየክልሉ ነጻ የሆኑ ትናንሽ መንግሥቶችን እንመሰርታለን፤ ደካማውን ማእከላዊ መንግሥት በአመጽ እያስፈራራንም ቢሆን የሚገባንን (ወይም ከሚገባን በላይ?) ኃብትና ሥልጣን እናገኛለን ብለው የሚያምኑ የአክራሪ ዘውጌ ፖለቲከኞችና በስሜት የሚጋልቧቸው የዘውጌ የሕብረተሰብ ክፍሎች ናቸው።

ሶስተኛው ኃይል ደግሞ፣ እንደ ሁለቱ ኃይሎች በተግባራዊ እንቅስቃሴው ጠንካራ ባይሆንም፣ የለውጥ ኃይሉን በፍጹም የማያምን፤ በመሰረታዊ መልኩ ከዚህ በፊት ከነበረው አቋም የተለየ ነገር ይዞ መምጣት የማይችል፤ አገራዊ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት እመሰርታለሁ ብሎ ቃል የገባውም ሕዝብን ለማታለልና በአዲስ ጭምብል የቀድሞውን ሥርዓት ለማስቀጠል የሚፈልግ ኃይል ነው ብሎ የሚያምን ነው። ይህ ሶስተኛው ኃይል የለውጥ ኃይሉ በደንብ ከመደላደሉ በፊት በመቃወም፥ የህዝብ ተቀባይነት እንዳያገኝ በማድረግና ለውጡን ለማስኬድ ብቃትም ሆነ ተአማኒነት የለውም በማለት የተጀመረውን ለውጥ ከግቡ ለማድረስ ከሁሉም የተውጣጣ የሽግግር መንግሥት ይፈጠር በሚል የራሱን አጀንዳ ለማራመድ የሚሞክር ኃይል ነው።

እነኝህ ሶስት ኃይሎች አንድ ላይ በጋራ ተቀናጅተው የሚንቀሳቀሱ ኃይሎች ባይሆኑም፣ አንዳንዴም እርስ በርስ የሚጋጩ ቢሆንም፣ መንግሥትን የማዳከም ፍላጎታቸው ስለሚያስተሳስራቸው በሂደትና በተለይም በሚያሰራጩት ፀረ-መንግሥት ፕሮፓጋንዳ ይደጋገፋሉ።

በነኝህ ሶስት ተደጋጋፊ ኃይሎች ግፊት በተፈጠሩት ቀውሶችና ግርግሮች መሀከል የምንፈልገውን እናገኛለን ብለው የሚያስቡት ኃይሎች በመጀመሪያ የምርጫው ጊዜ ከተቀመጠለት የጊዜ ሰሌዳ ዝንፍ ካለ አገር ቀውጢ ይሆናል ብለው ሲያስፈራሩ ቆዩ። ምንም እንኳን አብዛኛው የማህበረሰብ ክፍል አገር ተረጋግቶ ማዕከላዊው መንግሥትም ከግጭት ነጻ፣ ታዓማኒ፣ ፍትሃዊና በአጠቃላይ የዴሞክራሲያዊ ምርጫ መመዘኛዎችን የሚያሟላ ምርጫ የማካሄድ አቅም እስከሚያዳብርና ምርጫውን የሚያስፈጽሙ ተቋማትም እስኪጠናከሩ ድረስ፣ የምርጫው ጊዜ ትንሽ እንዲዘገይ የሚፈልግ ቢሆንም፥ ከዚህ በተጨማሪ መንግሥትም በምርጫው መራዘም "ተፎካካሪ ድርጅቶች የሚስማሙ ከሆነ ሀሳቡን ለማንሸራሸር ችግር የለብኝም" ያለ ቢሆንም፤ ምርጫው ካልተደረገ ችግር እንፈጥራለን ለሚሉ ኃይሎች ድንጋይ ላለማቀበል በመፈለግ ይመስላል ምርጫው በተያዘለት የጊዜ ሰሌዳ መደረግ አለበት ብሎ የወሰነው፡፡ ይህ ሲሆን ደግሞ፣ ምርጫው መራዘም አለበት በሚል ማንገራገር በተለይ ምርጫው ከተቀመጠለት የጊዜ ሰሌዳ ትንሽ ወራት አልፎ እንደሚካሄድ ሲነገርና የምርጫው መካሄድ የማይቀር መሆኑ ሲታወቅ እነኝሁ ለውጡን ለማደናቀፍ የሚፈልጉት ኃይሎች ምርጫውን ለማወክና ተአማኒነት ለማሳጣት በሙሉ ኃይላቸው መንቀሳቀስ ጀመሩ። ለመሆኑ እነዚህ ለውጡን ለማደናቀፍ የሚንቀሳቀሱት ኃይሎች ምርጫውን ለምን ፈሩት? ምርጫው መካሄዱ የማይቀር ከሆነና ምርጫው በርግጥም የህዝብ ፍላጎት የሚንፀባረቅበት ከሆነ የሚኖረው አንድምታ ምንድን ነው? ምርጫው በትክክለኛ መንገድ እንዳይካሄድ ከፊታችን የተደቀኑት ዋና ዋና ችግሮችና የችግሮቹ ፈጣሪዎች የትኞቹ ኃይሎች ናቸው?

## አሁን ለምን ወደ ምርጫ መሄድ አስፈለገ? የምርጫው ፋይዳስ ምንድን ነው?

ከላይ ከፍ ሲል የጠቀስኳቸው በመደበኛም ሆነ ኢመደበኛ በሆነ ስብስብ የተደራጁ ኃይሎች ሁሉ እንወክለዋለን የሚሉት ትልቅ ማህበረሰብ ወይንም ቆመንለታል የሚሉት አመለካከት አለ። ለምሳሌ በአንድ ዘውጌ ማህበረሰብ ስም የተደራጀ ቡድን የዚያን ዘውጌ ማህበረሰብ ጥቅም አስጠብቃለሁ ነው የሚለው። ወይም በአንድ የጋራ አመለካከት ዙሪያ የተሰባሰበ አገራዊ ቡድን ይህ አመለካከት ጠቅላላ ማህበረሰቡን ይጠቅማል ወይንም ቢያንስ አብዛኛው ማህበረሰብ የሚቀበለው ነው ብሎ ነው የሚንቀሳቀሰው። ነገር ግን በየትኛውም መለኪያ ቢለካ በአገር ደረጃ ቀርቶ በእያንዳንዱ ዘውጌ ማህበረሰብ ደረጃ እንኳን ሁሉም የዚያን ማህበረሰብ አባል አንድ አይነት አመለካከት ወይንም ፍላጎት አለው ለማለት አይቻልም። ያ ቢሆን ኖሮ ለአንድ የዘውጌ ማህበረሰብ አንድ የፖለቲካ ድርጅት ብቻ ይኖር ነበር። የኦሮሞን ህዝብ እንወክላለን የሚሉ ከደርዘን በላይ የፖለቲካ ድርጅቶች ወይንም የአማራ ህዝብን እንወክላለን የሚሉ ስድስት ድርጅቶች፤ ወይንም ደግሞ የኢትዮጵያን ህዝብ እንወክላለን የሚሉ በጥቅሉ ከመቶ በላይ ድርጅቶች ባልኖሩ ነበር።

በየትኛውም ማህበረሰብ ውስጥ አብዛኛው ሕዝብ የፖለቲካ ስብስቦች ዓባል አይደለም። በጠቅላላው በሀገራችን አሉ የሚባሉ ከመቶ አርባ የሚበልጡ የፖለቲካ ድርጅቶች በሙሉ ያላቸውን አባላት ብንደምር ከሀገሪቱ አጠቃላይ ሕዝብ 5% እንኳን አይደርሱም። ታዲያ የአብዛኛው ሕዝብ ፍላጎት ምንድን ነው? የትኛው የፖለቲካ ድርጅት ነው የብዙሀኑን ፍላጎት የሚያንጸባርቀው የሚለውን ጥያቄ እንዴት በእርግጠኛነት መመለስ እንችላለን? ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት በሌለበትና እውነተኛና ነጻ ምርጫ በማይደረግበት ሁኔታ ውስጥ ይህን የሕዝብ ውክልና ማወቅ የሚቻልበት መንገድ ስለሌለ የትኛውንም ድርጅት አንተ የሕዝብ ወኪል ነህ ወይንም አይደለህም ለማለት አይቻለም። መንግሥትም ግልጽ የህዝብ ውክልና ሳይኖረው

በጉልበት ወኪል ነኝ ብሎ ስለሚገዛ መንግሥትን የሚቃወመውም ከቻለ በጉልበት አለያም በቻለው አቅም ህዝቡ መንግሥትን እንዳይቀበል ለማድረግ በሚያደርገው ሙከራ የፖለቲካ ህልውናውና አቅሙ ይለካል።

ከላይ በመግቢያዩ ላይ እንደጠቀስኩት ይህ የለውጥ እንቅስቃሴ ሲጀምር የዚህ የለውጥ (የሽግግሩ) መዳረሻ የሚሆነው በነጻና ፍትሀዊ ምርጫ ያብዛኛው ህዝብ ውክልና ያለው የፖለቲካ ኃይል ስልጣን ሲይዝ ነው በሚል ቃል ኪዳን ነው። በሌላ አነጋገር የሚመሰረተው የመንግሥት ሥርዓት ዴሞክራሲያዊ ይሆናል፤ መንግሥት በህዝብ ነጻ ውክልና ብቻ ነው የሚመሰረተው፤ ይህንን ውክልና ለማረጋገጥ ደግሞ ነጻና ፍትሀዊ ምርጫ ይደረጋል፤ ነጻና ፍትሀዊ ምርጫ እንዲደረግ ደግሞ ሁሉም ሊከተለው የሚገባ፤ ለሁሉም እኩል የሆነና የዚህ ዓይነት ሥርዓትን ከመሰረቱ ሀገሮች ልምድ ለተቀዳ "የጫወታ ሕግ" ሁሉም የፖለቲካ ኃይሎች ተገዢ ይሆናሉ፤ ከዚህ ውጭ የሚገኝ ውክልና ብሎ ነገር የለም፣ የሚል ስምምነት ላይ ተደረሰ ነበር።

ገና ለውጡ በተጀመረ የመጀመሪያዎቹ ወራት ሁሉም የፖለቲካ ድርጅቶች በጋራ ተወያይተው በፈቃደኝነት ያጸደቁትና የተፈራረሙበት "የስነ ምግባር መመሪያ ቃልኪዳን" ይህን የጨዋታ ሕግ በግልጽ ያስቀምጣል። ይህም ማለት ሁሉም የፖለቲካ ፓርቲዎች ምን ያህል የህዝብ ውክልና እንዳላቸው ሊታወቅ የሚችለው በነፃ ምርጫ፤ ህዝቡ ይወክሉኛል ብሎ በሚመርጣቸው ጊዜ ብቻ ነው። ሕዝቡ ደግሞ ማን በርግጥ ይወክለኛል ወይንም ጥቅሜን ያስጠብቅልኛል ብሎ በስሜት ሳይሆን አስቦ መምረጥ የሚችለው እነኝህ የተለያዩ ድርጅቶች የቆሙለትን አላማ፤ ፕሮግራም ወይንም አማራጭ ፖሊሲዎች ካቀረቡለት በኋላ ይህንን ሁሉ ሰምቶ ለኔና ለቤተሰቤ ብሎም ለአገሬ የሚጠቅመው የትኛው ነው? ብሎ የሚያምነውን ያለምንም መሳቀቅ ወይንም ፍርሀት የሚመርጥበት ሁኔታ ሲመቻችለት ብቻ ነው። ከዚህ ውጭ በጉልበት፤ በማስፈራራት፤ በብጥብጥ ወይንም በሌላ መልክ የሚገኝ "ውክልና" ተቀባይነት አይኖረውም። እንዲህ ዓይነት ነጻ ውክልና ሳይገኝ አለ የሚባል ውክልና ሁሉ ተጨባጭነት የሌለው የጨበጣ ውክልና ነው። ለዚህ ነው ይህ ምርጫ አንዱ ትልቁ ፋይዳው በሰላማዊና ፍትሃዊ በሆነ መንገድ ከተካሄደ ከነኝህ ሁሉ እስካሁን በጨበጣ "የሕዝብ ወኪል ነን" ብለው ከሚርመሰመሱና በሕዝብ ስም የተለያዩ ትርምሶችን ከሚፈጥሩ ድርጀቶች ውስጥ የትኞቹ በእርግጥም ምን ያህል የሕዝብ ውክልና አላቸው የሚለውን በማያሻማ ሁኔታ መመለስ መቻሉ ነው። ሕዝብ አንዴ ይወክለኛል የሚለውን ከመረጠ በኋላ እነኝህ በህዝብ የተወከሉ ድርጅቶች በግላቸውም ሆነ በጋራ በተቀመጠው የጨዋታ ሕግ መሰረት የመረጣቸውን ህዝብ ጥቅም ለማስጠበቅ የሚያደርጉት ሰላማዊ እንቅስቃሴ ትክክለኛ፥ ፍትሀዊና ቅቡልነት ያለው ይሆናል። በተመረጡበት የጊዜ ዘመን ይህ ህዝብ የሰጣቸውን የውክልና አደራ ባግባቡ ካልተጠቀሙበት፤ ማህበረሰቡ እነሱን ሽሮ ሌላ የተሻለ የሚለውን የመምረጥ መብት ስላለው የተመረጠውም መንግሥት እንደፈለገ ህዝቡን የሚረግጥ አምባገነን ሳይሆን በህዝብ የምርጫ ኃይል የተገራ ይሆናል፤ ይህ ብቻ ሳይሆን በህዝብ የተመረጠው መንግሥት የህዝብን ፈቃድ ያገኘ ስለሚሆን ለሚተገብራቸውም ፕሮግራሞች የህዝብ ድጋፍ ስለሚኖረው ጠንካራ፤ ቅቡልነት (legitimacy) ያለውና ተቋማዊ መሰረት የያዘ ይሆናል። ይህ ከተሳካልን፤ በአገራችን ያሉትን ችግሮች ሁሉ ባንድ ጊዜ ቀርፈናል ማለት ሳይሆን ከላይ የጠቀስኩትን የሥልጣኔ ሂደት በተረጋጋ ማህበራዊ መሰረትና ስምምነት ጀምረን፤ ወደፊት እያየን ሌሎቹን የተጠራቀሙ ችግሮች በሠለጠነ መንገድ የመፍታት ሂደት እንጀምራለን ማለት ነው።

ይህንን ማድረግ ካልቻልን ግን ውጤቱ ምን ሊሆን እንደሚችል ባለፉት 18 ወራት ያየናቸውና ማህበረሰባችንን ጭንቀት ውስጥ የከተቱት ችግሮች እጅግ በጣም በገዘፈ መልኩ የሚከሰቱበትና ወደ አጠቃላይ ቀውስ የምንገባበት ሁኔታ መፈጠሩ አይቀሬ ይሆናል። ውክልናቸው በህዝብ ያልተረጋገጠላቸው "ወኪል ነን" ባይ ድርጅቶች "ውክልናቸውን ለማረጋገጥ"

ሊሄዱበት የሚችሉት ብቸኛ መንገድ ጉልበትና አመጽ ብቻ ይሆናል። ይህ አመጽ ደግሞ አንድ ኃይል ወይም አንድ ወገን ብቻ የሚያካሂደው አመጽ ሳይሆን ሁሉም ሁሉንም የሚፈራበት፤ ሁሉም ከፍርሀቱ ለመውጣት ሳልቀደም ልቅደም በሚል እራሱን ለአመጽ የሚያዘጋጅበት፤ ተዘጋጅቶም “ጠላቴ” የሚለውን ኃይል ለማጥፋት የሚንቀሳቀስበት፤ የዘውጌ ክልሎች አንዱ ካንዱ ጋር ለውጊያ የሚነሳሱበት፤ በዘውጌ ክልሎችም ውስጥ (ህገ-መንግስቱ ባመጣው መዘዝ ነባር ኗሪ/ የክልል ባለቤቶች በሚባሉትና መጤ በሚባሉት ኢትዮጵያውያን መካከል ግጭት መቀስቀሱ አይቀርም)፤ በየአካባቢው ባሉ ጊዜው የኛ ነው ባይ ጉልበተኞች (የጦር አበጋዞች) የሚመሩ ቡድኖች የበላይነት ለማግኘት የዕርስ በዕርስ ጦርነት ውስጥ የሚገቡበት እልም ያለ ሥርዓት አልበኝነት የሚነግሥበት ሁኔታ መፈጠሩ አይቀሬ ነው።

ከዚህ የተለየ አማራጭ አለ ብለን ብናስብ እንኳን እንዲህ ዓይነቱ  የዕርስ በዕርስ መጠፋፋትና ሥርዓት አልበኝነት ለደህንነቱ ስጋት የሚሆንበት ማህበረሰብ “ከዚህ ዓይነቱ ትርምስ” ይልቅ ጠንካራ አምባገነን ቢገዛን ይሻላል በሚል የመንግሥትን ሥልጣን የያዘው ኃይል ሌላውን በጉልበት እንዲጨፈልቅ ፈቅዶና በመንግሥት ስልጣን ላይ ያለውም ኃይል “የፖለቲካ ኃይሎች ሀገርን ትርምስ ውስጥ ሲከቷት እጄን አጣጥፌ አላይም” በሚል የማህበረሰቡን ፍርሀት በጉልበት ሥልጣን ላይ ለመቆየት ይጠቅምበታል። እነዚህ ሁለት አማራጮች ዘላቂ የሆነ ሰላምና የተረጋጋ፤ ወደፊት የሚያይ፤ ማህበረሰብ እንዳንፈጥር ያደርጉናል እንጂ መፍትሄ አይደሉም። ይህ የተያያዝነው የለውጥ ሂደት ከዚህ በፊት እንደነበሩት የለውጥ ሙከራዎች ከስሞ በ21ኛው ክፍለ ዘመን ሌሎች ማህበረሰቦች የደረሱበት  ስልጣኔ ሂደት አካል ከመሆን ይልቅ ከመቶዎች ዓመታት በፊት ወደነበርንበት የጨለማ ዘመን መልሶ የሚከተን ከሆነ አደጋው ወደኋላ መመለስ ብቻ ሳይሆን እንደ አገር መቀጠል አለመቻልም ሊሆን ይችላል።

## ይህ ምርጫ ለችግሮቻችን መፍቻ መነሻ እንዲሆን ምርጫው በምን መልክ መካሄድ አለበት?

ተመልሰን ወደ “ጨለማ ዘመን” እንዳንሄድ ይህ ምርጫ በጣም አስፈላጊ ነው በሚለው ከተስማማን፤ ምርጫው ደግሞ ከላይ በጠቀስኳቸው ምክንያቶች መደረጉ የማይቀር ከሆነ፤ ከዚህ በፊት ምርጫዎች ብናደርግም ነፃ፥ ፍትሃዊ የሆነና ተዓማኒነት ያለው ምርጫ ማድረግ እንዳልቻልን ካወቅን፤ ይሄኛው ምርጫ የህዝብ ውክልና የሚንፀባረቅበትና ተዓማኒነት ያለው ምርጫ እንዲሆን ምን ዓይነት መስፈርቶች መሟላት አለበት? እንዲህ ዓይነት ምርጫ ለማድረግስ ከፊታችን የተጋረጡ ፈታኝ አገራዊ አደጋዎች ምንድን ናቸው? ወደሚለው የዚህ መልእክቴ ዋና ጉዳይ  እገባለሁ።

ምርጫው ተአማኒ እንዲሆንና የህዝብ እውነተኛ ፍላጎት መገለጫ እንዲሆን መሟላት ያለባቸው ጉዳዮች ግልጽና ብዙ የማያከራክሩ ናቸው። ሰላም መኖር አለበት፤ ሰላም በሌለበት ህዝብ እውነተኛ ፍላጎቱን የሚገልጽበት ድባብ አይኖርም። ህዝብ የሚፈልገውን እንዲመርጥ፤ የቀረቡለት አማራጮች ምን መሆናቸውን በውል ማወቅ አለበት። ህዝብ አማራጮቹን እንዲያውቅ ደግሞ የተለያዩ የፖለቲካ ድርጅቶች ያለምንም ፍርሃትና መሸማቀቅ አማራጭ ሃሳቦቻቸውን የሚያቀርቡበትና ሕዝቡ አማርጦ የሚሰማበት ሁኔታ መፈጠር አለበት። በሌላ አነጋገር አማራጭ አለን የሚሉ ድርጅቶች በየትኛውም የአገሪቱ ክፍል ያለምንም ችግር ማህበረሰቡን ሰብስበው ማናገር መቻል አለባቸው። መራጩ ህዝብ የሚፈልገውን ስለመረጠ ምንም ዓይነት የደህንነት አደጋ አይደርስብኝም ብሎ መተማመን ደረጃ ላይ መድረስ አለበት።

ይህ ብቻ ሳይሆን በምርጫው ሂደት የመንግሥት የፀጥታ ኃይሎች ምርጫው በሰላማዊ መንገድ እንዲካሄድ ከማድረግ በስተቀር ለማንኛውም ተወዳዳሪ ኃይል አግዘው እንደማይቆሙ ማረጋገጥና ዋስትና መስጠት ይፈልጋል። ከዚያም ባሻገር ህዝብ በምርጫ የሰጠው ድምፅ በትክክል እንደሚቆጠርና እንደማይጭበረበር ህዝቡ ማመን አለበት፡፡ መምረጡ በምርጫው ሂደት ላይ ትርጉም እንዳለው ሲያምን በነቂስ ወጥቶ የምርጫ ካርድ ያወጣል፤ በምርጫው ዕለት ደግሞ ጥቅሜን ያስከብሩልኛል ላላቸው ፓርቲዎች ድምፁን ይሰጣል። ስለዚህ ምርጫውን የሚያካሂደው አካል (ማለትም ምርጫ ቦርድ) ፍፁም ነፃና ገለልተኛ እንደሆነ፤ በምርጫው ሂደት መሰናክሎች ቢገጥሙ ይህንን ለማንም ሳያዳላ የሚያይና የሚፈርድ፤ ተአማኒነት ያለው የዳኝነት/የፍትሕ ሥርዓት እንዳለ ማወቅ ይፈልጋል። እነኝህና ሌሎችም የታወቁ ምርጫውን ነፃና ለሁሉም እኩል በሆነ የመወዳደሪያ ሜዳ የሚደረግ ውድድር መሆኑን የሚያረጋግጡ ተቋማዊ ተግባራት በትክክል መሠራታቸው እጅግ አስፈላጊ ነው። እነኝህ ናቸው ምርጫውን በእርግጥም ተአማኒ የሚያደርጉትና የምርጫውንም ውጤት ተቀባይነት የሚሰጡት። እነኝህ መሟላት ያለባቸውን ሁኔታዎች ለትክክለኛ ምርጫ አስፈላጊ መሆናቸውን ቢያንስ በንድፈ ሀሳብ ደረጃ የማይቀበል፤ የዴሞክራሲን ሀሁ አውቃለሁ የሚል አንድም የፖለቲካ ድርጅት ወይንም ግለሰብ ሊኖር አይችልም።

ዋናው ጥያቄ ታዲያ፤ እነኝህ ነገሮች አስፈላጊነታቸው ላይ ሰፊ ስምምነት ካለ፤ ይህን በተግባር ለመተርጎም በአገራችን የሚያስቸግረው ለምንድን ነው? ወይንም ይህ ሂደት ከላይ በተቀመጠው መልኩ እንዳይካሄድ እንቅፋት ሊፈጥሩ የሚችሉት ኃይሎች ምን ዓይነት ኃይሎች ናቸው? የሚለውን ተጨባጭና ተግባራዊ ጥያቄ በአጥጋቢ ሁኔታ መፈተሽ ያስፈልጋል።

## ለምርጫው ሳንካዎች ከየት ሊመጡ ይችላሉ?

ይህን ለመመለስ እኛ እንደድርጅት በተለያዩ ክልሎች በተንቀሳቀስንባቸው ቦታዎች ያጋጠሙንን ሳንካዎች በወሬ ደረጃ ሳይሆን በተጨባጭ ነቅሰን ማመላከት እንችላለን። እነኝህን ሳንካዎች ገና የምርጫው ሂደት ከመጀመሩ በፊት ማንሳት የፈለግነው አሁን በየአካባቢው የምናያቸው መሰናክሎች ከወዲሁ መልክ ካልያዙ፤ የምረጡኝ ዘመቻ ሲጀመር ከሚፈጠረው ስሜታዊነት ጋር እየባሱ እንደሚሄዱ፥ በዚህም ለበለጠ ግጭት ሊዳርጉን እንደሚችሉና የምርጫውን አጠቃላይ ሂደትና ውጤት ተአማኒነት ጥያቄ ውስጥ ሊከቱት እንደሚችሉ ከወዲሁ ለማስታወስ ነው። የምርጫው ሂደት በህዝቡ እይታ ጥያቄ ውስጥ ከገባ ከላይ እንደጠቀስኩት አገራችን ወደ ሥርዓት አልበኝነት ወይም ወደ ሌላ አምባገነናዊ አገዛዝ የመግባት እድሏ ከፍተኛ ይሆናል። እኛ በተግባር ከታዘብነው የምርጫውን ሰላማዊነትና ፍትሀዊነት ሊያውኩ የሚችሉ እንቅስቃሴዎች ከሶስት ዓይነት ኃይሎች ሊመጡ ይችላሉ። ለመሆኑ እነዚህ ኃይሎች እነማን ናቸው፤ እንዴትስ የምርጫውን ሰላማዊ ሂደት ሊያስተጓጉሉ ይችላሉ የሚለውን ለየብቻ እንመልከታቸው፤

## ሀ) በብሄር የተደራጁ ጽንፈኛ ኃይሎችና በስራቸው የተሰባሰቡ ኢ-መደበኛ የሕብረተሰብ ክፍሎች፤

በብሄር የተደራጁ ኃይሎች የሚይዙት መልክ ከቦታ ቦታ ይለያይ እንጂ፣ እነዚህ ኃይሎች የሚፈጥሯቸውን ችግሮች በሶስቱም ትላልቅ የአገሪቱ ክልሎች (በኦሮሚያ፣ በአማራና በደቡብ) ተመልክተናል። ዋና መለያቸው እነሱ "ክልላችን" በሚሉት አካባቢ ከሚያራምዱት አመለካከት ውጭ ያለን ማንኛውንም አመለካከት ወይንም ድርጅት ላለመስማት በመፈለግ፣ ወይንም ህዝቡ እንዳይሰማ ለመከላከል የሚያደርጉት እንቅስቃሴ ነው።

በቅርቡ በደብረ ብርሃንና በጎንደር ኢዜማ ያዘጋጃቸውን ህዝባዊ ስብሰባዎች ህግን በመጣስና የህዝብን ፍላጎት በመርገጥ ታዳሚው ወደ አዳራሽ እንዳይገባና ከገባ በኋላም ምንም ዓይነት ውይይት እንዳይካሄድ በጩኸት በማስቆም፤ የመጣውን ህዝብ በማስፈራራትና ግጭት እንዲፈጠር የገፋፉ ኃይሎች እራሳቸውን ኢ-መደበኛ በሆነ መንገድ ያደራጁ ስብስቦች ናቸው። ከዚህ በፊትም ተመሳሳይ ስብስቦች በባህር ዳር ከተማ በጦር መሳሪያ የታገዘ የስብሰባ ማደናቀፍ እንቅስቃሴ ማድረጋቸው የሚታወስ ነው። እነዚህ ወጣቶች አዳራሹ ውስጥ ገብተው በሰላማዊ መንገድ የውይይቱ ተሳታፊ እንዲሆኑ፤ ጥያቄ ካላቸውም በሥርዓት እንዲጠይቁ ቢጋበዙም ፈቃደኛ አልሆኑም። ወጣቶቹ ይህን የሚያደርጉት አማራን ይጠቅማል ብለውና በአማራ ብሄረተኛነት ተደራጅተው ነው። ወደ ስብሰባዎቹ መጥቶ አማራጭ ሃሳቦችን እንዳይሰማ የሚከላከሉትም ባብዛኛው እንወክለዋልን እንደዚሁም ጥቅሙን እናስከብርለታለን የሚሉትን የአማራን ህዝብ ነው። በአማራ ክልል የተደረጉትን ስብሰባዎችና ከስብሰባዎቹ ጋር ተያይዞ የታየውን ረብሻ ከሌላው ትንሽ ለየት የሚያደርገው የዚህ አይነት ሁከት ሲካሄድ የከተማው ፖሊሶችና የክልሉ ልዩ ኃይል በሕግ የተፈቀደ ስብሰባ ሲበጠበጥ ሕግ የማስከበር ሕገ-መንግስታዊ ግዴታቸውን ለመወጣት ምንም አይነት ፍላጎት አለማሳየታቸው ነው፤ ጭራሽ ስብሰባው ሊከናወን በተዘጋጁበት አዳራሽ የነበረውን የስርዓት-አልበኝነት ክስተት ቆመው ማየታቸው ነው። ሌላው አስገራሚ ነገር ተሰብሳቢው ሕዝብ በሕግ የተሰጠውን ሀሳቦችን የመስማት መብት አትከለክሉኝም ብሎ ከጎረምሶቹ ጋር ግጭት ውስጥ ቢገባ እነኝህ የታጠቁ የከተማና የክልል የጸጥታ ኃይሎች "ሰላምን ለማስከበር" በሚል ሰበብ ስብሰባው እንዳይደረግ እንደሚያስቆሙት መገመት በፍፁም አያስቸግርም።

እንደዚህ ዓይነት ክስተት ለኦሮሞ ህዝብ ቆመናል የሚሉ ህገወጥ የወጣቶች እንቅስቃሴዎች ከዚህ በፊት በጅማና አንድ ጊዜ ደግሞ እዚሁ በአዲስ አበባ ዉስጥ ለድርጅታችን አባላት ብቻ በተዘጋጀ የውይይት መድረክ ላይ መከሰቱም ይታወሳል። ከሁለት ወር በፊት በአዳማ ከተማ ባካሄድነው ሕዝባዊ ውይይት ላይም በተመሳሳይ ኃይሎች ስብሰባውን ለማወክ የተደረጉ ጥረቶች በተሰብሳቢዉ አልቀበልም ባይነትና በወቅቱ አዳራሹ ውስጥ የነበሩ የፀጥታ አስከባሪዎች በወሰዱት እርምጃ ከሽፏል። በሀዋሳ ደግሞ የተደረገው ከዚህ ትንሽም ቢሆን ለየት ያለ ነበር። የሲዳማን ሕዝብ እንወክላለን የሚሉ ወጣቶች ተደራጅተው ስብሰባ ውስጥ ገብተው የመጀመሪያውን ንግግር በጥሞና አዳምጠው (ሌላው ተሰብሳቢ በቁጥር በጣም ብዙ ስለነበርና የፀጥታ አስከባሪዎች ረብሻ እንዳይፈጠር በቅርብ ይከታተሉ ስለነበር ጉባዔውን ለመረበሽ አይቻልም ነበር)፤ ነገር ግን በጥያቄና መልሱ ጊዜ በተወካያቸው በአንዲት ወጣት ሴት የተዘጋጁበትን ንግግር በጥያቄ መልክ አቅርበው መልሱን ሳይሰሙ ስብሰባውን ጥለው ወጥተዋል። የዚህ አይነት ስብሰባ መበጥበጥ የህዝብ ፍላጎት እንዳልሆነ በስብሰባው የተገኙ የሲዳማ ሽማግሌዎች ድርጊታቸው በፍፁም የሲዳማን ህዝብ የማይወክል ዋልጌነት እንደሆነ ለተሰብሳቢው በሲዳምኛ ተናግረዋል።

እነኝህ ሁሉ እንቅስቃሴዎች አንድ ኢላማ አላቸው። እነሱ ከሚያስቡት ሌላ ምንም አይነት የተለየ አመለካከት "የኛ ነው" በሚሉት ክልሎች ውስጥ ሰሚ እንዳያገኙ ማወክና ህዝቡ ምርጫ ላይ ሲመጣም ያለምንም አማራጭ የነሱን ሀሳብ ብቻ ሰምቶ ወይንም ፈርቶ "ሳያምንበትም ቢሆን እንዲመርጣቸው" ማድረግ ነው። የዚህ አካሄድ ዋና ሰለባ ደግሞ የዚያው "እንወክለዋለን/ጥቅሙን ለማስከበር እንታገልለታለን የሚሉት" የአካባቢው ሕዝብ ነው። በእነዚህ ህገወጥ ስብስቦች መሰረታዊ መብታቸው የሚጣሰው ስብሰባውን ያዘጋጁት የአካባቢው ተወላጆች የሆኑ የድርጅታችን አባላት ብቻ ሳይሆኑ ፓርቲያችን ያለውን ሐሳብ ለመስማት የመጣው ሕዝብ ጭምር ነው። ይህ ሁኔታ ዛሬ ከዘውጋዊ አደረጃጀት ውጭ አገራዊ አመለካከት ባላቸው ኃይሎች ላይ የሚደርስ "የአክራሪ ብሄረተኞች" ኢ-ዴሞክራሲያዊ አካሄድ ቢመስልም ጉዳዩ በራሳቸው በክልሎች ውስጥ ባሉ የተለያየ አመለካከት ባላቸው ብሄርተኞች መሀል በየመንደሩ እየተመነዘረ ግጭት መፍጠሩ የማይቀር

መሆኑንና ለዚህም ከበቂ በላይ ምልክቶችን እያየን መሆኑ ነው። በቅርቡ በኦሮሚያ ክልል በጅማና በተፍኪ ከተሞች በሁለት የኦሮሞ ብሄረተኛ ድርጅት ደጋፊዎች መሀል "እኔ እያለሁ ሌላ ድርጅት እዚህ አካባቢ ቢሮ መክፈትም ሆነ ሕዝብ ማደራጀት አይችልም" በሚል የተፈጠረ ሁከት በአካባቢው የፀጥታ ኃይሎች በተኩስ እስከሚበተን ድረስ የደረሰውን ጉዳት የቅርብ ጊዜ ትውስታችን ነው።

እንዲህ ዓይነቱ አካሄድ በቶሎ ካልተገደበ በምርጫው ሂደት ላይ የሚያመጣው ችግር ብቻ ሳይሆን በዚህ ከቀጠለ በአገራችን ህልውና ላይ የሚያመጣውን አደጋ ለማየት እነኝህ ኃይሎች ይህን የሚያደርጉት ለምንድን ነው? ምንስ ፈልገው ነው የሚለውን ጥያቄ መመለስ ያስፈልጋል።

መቼም እንዲህ አይነት አካሄድ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ለማምጣት በሚፈልጉ ኃይሎች የሚደረግ እንዳልሆነ ግልጽ ነው። ይህንን የሚያደርጉ ኃይሎች በዋናነት የሚሹት እነሱ "የእኛ" ብለው በሚያምኑት ክልል ውስጥ የሚኖረው ህዝብ ከነሱ ዉጭ ሌላ ምንም አይነት ሃሳብ እንዳይሰማ መከላከልና "የእኛ" የሚሉትን ክልል ያለተቀናቃኝ ጨፍልቀው መግዛት እንዲችሉ በማሰብ ነው። በእነሱ እምነት "የእኛ" ነው በሚሉት ክልል ያለው ህዝብ ሁሉ ቋንቋውና ባህሉ ብቻ ሳይሆን አስተሳሰቡም አንድ መሆን አለበት ወይም የአንድ ክልል ህዝብ ከሌላው ኢትዮጵያዊ ጋር የሚያገናኘው ምንም ክር መኖር የለበትም፣ እንዲያውም በእነሱ አመለካከት እንዲህ ዓይነቱ አንድ ህዝብ ከሌላው ህዝብ ጋር ያለው ማኅበራዊ መተሳሰር የክልሉን "ዘውጋዊ ማንነት" የሚቀናቀን "ፀረ-የዚያ ዘውግ" አመለካከት ነው። የእነሱ ዘውግ አባል ሆኖ የነሱን መንገድ የማይከተል ግለሰብ ሁሉ "ዘውጉን የከዳ" ከሀዲ ነው፤ ስለዚህም በዚያ ዘውጌ ክልል ውስጥ ምንም መብት ሊኖረው አይገባም። በእነሱ እምነት የእነሱን የዘውጌ መንገድ ያልተከተሉ ዜጎችን ሰብዓዊ መብት መጣስና ማንቋሸሽ ተገቢና ተቀባይነት ያለው አካሄድ ነው። ይህ የተዛባ አስተሳሰብ ጭራሽ የተለያዩ ብሔር ካላቸው ወላጆች የተወለዱ ግለሰቦችን ንፁህ ያልሆኑ (ቅይጥ) በማለት በማግለል በተወለዱበት፣ ባደጉበትና በሚኖሩበት ማህበረሰብ ውስጥ እንደታማኝ አባል ባለመታየታቸው ከፍተኛ መገለልና መድሎ እንዲደርስባቸው መንስዔ እየሆነ ይገኛል፡፡

***ወገኖቼ ይታያችሁ!***

እንዲህ አይነት አመለካከት ያላቸው ሰዎች እነሱ ያላሸነፉበትን ምርጫ ምንም ያህል ነፃና ፍትሃዊ ቢሆን እንኳን ውጤቱን ይቀበሉታል ወይ የሚለው ነገር አሳሳቢ ነው፡፡ በለስ ቀንቷቸው ምርጫውን ቢያሸንፉ በክልላቸው ውስጥ ዴሞክራሲያዊ አስተዳደር ይመሰርታሉ ወይ? በዚህስ መልክ እንኳን በአገር ደረጃ በአንድ ክልል ውስጥስ እንዴት ሆኖ ነው ሰላምና መረጋጋት የሚፈጠረው? እንዲህ አይነቱ አደገኛ አካሄድ ሲኖር በክልሉ ውስጥ ለሚኖሩ የሌላ ክልል ነዋሪዎች (በነሱ አጠራር መጤ/ሰፋሪዎች) ቀርቶ የተለየ አመለካከት ያለው ከራሳቸው ዘውግ የሆነ ነዋሪ እንዴት ነው በሰላም ስራ ውሎ በሰላም ወደቤቱ የሚገባው?

የህወሓት/ኢህአዴግን ሥርዓት ለመጣል በተደረገው ትግል የተሳተፉ ኃይሎች፤ በተለይም ዘውጌ ብሄርተኞች ሁሉ የቀድሞውን ሥርዓት የሚኮንኑት ህገ-መንግስቱ ቋንቋና ማንነትን ብቻ እንደ ዋና መመዘኛነት ወስዶ ዘጠኝ አሐዳዊ የሆኑ ክልሎችን መሸንሸኑን አይደለም፥ ይልቁንም የክልሎች መፈጠር "ብሄር ብሄረሰቦች" ቋንቋቸውን የማበልጸግና ባህላቸውን

የመንከባከብ መብት ሰጥቷል ብለው ስለሚያምኑ ዋነኛው የተቃውሞ መሰረታቸው የፌደራሊዝም ዋና መሰረት የሆነው የብሄሮች የራስን በራስ የማስተዳደር መብት አልተከበረም የሚል ነው። ዴሞክራሲ ከሚለካበትና ፌዴራላዊ ሥርአቶች ከሚመዘኑበት ትላልቅ እሴቶች ውስጥ አንዱና ዋናው ህዝብ በሚኖርበት አካባቢ ሁሉ እራሱን በራሱ ማስተዳደር መቻሉ ነው።

ህዝብ በሚኖርበት የአስተዳደር እርከን ሁሉ እራሱን በራሱ ማስተዳደር አለበት የሚለውን መሰረተ ሃሳብ በግልጽ የሚቃወም የፖለቲካ ኃይል በዛሬይቱ ኢትዮጵያ የለም። ልዩነት ያለው ያልተማከለ ፌደራላዊ አስተዳደር ሲባል በተጨባጭ ምን ማለት ነው የሚለው ጥያቄ ላይ ነው። በየትኛውም ፌደራላዊ የመንግስት አደረጃጀትን በሚከተሉ አገሮች ውስጥ ያልተማከለ አስተዳደር ማለት ከታችኛው የአስተዳደር እርከን ጀምሮ (ቀበሌ፣ ወረዳ፣ ዞን፣ ክልል) ያሉ የመንግሥት አስተዳደሮች ሁሉ በአካባቢው ነዋሪ በተመረጡ መሪዎች ይተዳደራሉ ወይም አካባቢውን የሚመለከቱ አስተዳደራዊም ሆነ የልማት ውሳኔዎችን በህዝብ በተመረጡ መሪዎች ይወሰናሉ። ኢትዮጵያ ውስጥ ግን በብሄር የተደራጁ ኃይሎች ይህንን ለዘመናት "ታግለንለታል" የሚሉትን መርህ እንኳን በተግባር ለማዋል ፈቃደኞች አይደሉም። በእነሱ አመለካከት ያልተማከለ አስተዳደር ምን ማለት እንደሆነ ለማሳየት በሀዋሳው የኢዜማ ስብሰባ ላይ  የሲዳማን ወጣቶች እወክላለው ብላ ሀሳብ ያስተላለፈችውን እህት መልዕክት መጥቀሱ ይበቃል።

በሀዋሳው ስብሰባ ላይ የኢዜማ ተወካዮች ስለ ፌደራሊዝም ድርጅቱ ያለውን አመለካከት ከዚህ በላይ በጠቀስኩት መልክ ለተሰብሳቢው ያቀርባሉ። ይህች ወጣት በዚህ በጣም ተበሳጭታ እንዲህ ነበር ያለችው "እናንተ ትላንት ኢትዮጵያ፤ ኢትዮጵያ እያላችሁ ስትጮሁ ከርማችሁ አሁን ደግሞ ቀበሌዎችም የቀበሌው ህዝብ በመረጣቸው ሰዎች ይተዳደሩ ትላላችሁ፤ ይህ እኮ ማለት የናቴን ቤት ተከራይተው የሚኖሩ ሰዎች በተከራዩት ቤት የማዘዝ መብት አላቸው እንደማለት ነው፤ ይህ በፍፁም አይታሰብም" የሚል ንግግር አድርጋ፤ ጓደኞቿን አስጨብጭባ ስብሰባውን ከጓደኞቿ ጋር ረግጣ ወጣች። እንግዲህ በሷና በጓደኞቿ አመለካከት ከሲዳማ ብሄር ውጭ የሆነው ሀዋሳ ውስጥ የሚኖር  ኢትዮጵያዊ ሁሉ ሀዋሳ ውስጥ  የሚኖረው እንደ ቤት ተከራይ ስለሆነ አከራዩ (በእሷ አተያይ ሙሉ የሲዳማ ብሄር ተወላጅ የሆነው) በፈለገው ጊዜ የሚያባርረው፤ ምንም አይነት የዜግነት መብት የሌለው ሰው ነው ማለት ነው። ለመሆኑ እንዲህ አይነት አስተሳሰብ በነገሰበት አገር ውስጥ የተለያየ የዘውግ ማንነት ያላቸው ህዝቦች አገራዊ አንድነት ፈጥረው በሰላም አብሮ መኖር ይችላሉ? የአንድ አገር ዜጎች በሚኖሩበት አካባቢ ሰርተውና ላባቸውን አፍስሰው ያፈሩትን ኃብትና ከሚኖሩበት አካባቢ ነዋሪዎች ጋር ተጋብተው ወልደው የመሰረቱትን ትዳርና ኑሮ የነገ ዋስትና ከሌለው እንዴት ሆኖ ነው እራሳቸውን የዚህ አገር ዜጋ ነኝ ብለው የሚጠሩት? ይህ ዓይነት አመለካከት ከነገሰና ተቋማዊ መሰረቱን እያጠናከረ ከሄደ ነገ ከዚህ በፊት እንዳየነው አይነት አስከፊ የዜጎች መፈናቀል በስፋት ላለመደገሙ ምን ዋስትና አለን?

## ለ) በየክልሉና በተለይ በታችኛው እርከን ያሉ የመንግሥት አስተዳዳሪዎችና የፀጥታ ኃይሎች የሚፈጥሯቸው እክሎች፤

ሁለተኛውና በጊዜ ካልታረመ የምርጫውን ሂደት ከወዲሁ አደጋ ላይ የሚጥለው በየክልሉ በታችኛው እርከን ላይ የሚገኙ የመንግስት ባለስልጣኖች በአካባቢያቸው ከእነሱ የተለየ አመለካከት ያላቸውንና ምናልባትም በምርጫ ወቅት ሊቀናቀኑንና

ከስልጣናችን ሊያስነሱን ይችላሉ የሚሏቸውን ኃይሎች በነፃነት እንዳይደራጁና ከህዝቡ ጋር እንዳይገናኙ ለማድረግ ከወዲሁ የሚፈጥሯቸው እክሎች ናቸው። በእኛ አመለካከት በታችኛው የስልጣን እርከን ያለው የመንግሥት አካል የሚሰራቸው ስሯዎች ሁሌም በላይኛው እርከን የታወቁና የነሱን ይሁንታ ያገኙ እንዳልሆኑ የሚያሳዩ መረጃዎች አሉን፡፡ እነዚህ በታችኛው እርከን ላይ የሚገኙ የመንግሥት ባለስልጣናት እላይ ካለው የፌደራሉ መንግሥት ለይቶ ማየት በተወሰነ ደረጃ አስፈላጊ ነው። ይህን አቋም ለመያዝ የቻልነው በአንዳንድ ቦታዎች የወረዳና የዞን አስተዳደሮችና የፀጥታ አካላት ከላይ በመጀመሪያው ክፍል ከጠቀስኳቸው የፖለቲካ ኃይሎችና ኢ-መደበኛ የወጣት አደረጃጀቶች ጋር በመናበብ ህዝባዊ ስብሰባዎችን የማሰናከል እርምጃዎች ሲወስዱ በተደጋጋሚ ስላየን ነው።

እነኝህ የታችኛው መስተዳደር አካላት በአካባቢያቸው ያለውን "የመንግሥት ስልጣን" ይቀናቀኑናል ብለው የሚጠረጥሯቸውን ድርጅቶች በነፃነት እንዳይንቀሳቀሱ የተለያዩ እንቅፋቶችን ሲፈጥሩ በሁሉም ክልሎች አይተናል። በትግራይ ክልል ከህወሓት ውጭ ያሉ ድርጅቶችን ማወከ፤ የተፎካካሪ ድርጅት አባሎችን ማሰርና ማንገላታት በተደጋጋሚ የሰማናቸው ጉዳዮች ናቸው። በአንዳንድ የኦሮሚያና የደቡብ ክልል የአካባቢ መስተዳደሮች የማይደግፏቸውን የፖለቲካ ድርጅቶች ቢሮ እንዳይከፍቱ መከልከል፤ ቤታቸውን ለቢሮ አገልግሎት ሊያከራዩ የሚፈልጉ ባለሀብቶች የግል ንብረታቸውን እንዳያከራዩ ከፍተኛ ጫና መፍጠር፤ እኛ እንደ ድርጅት የደረሱብን ችግሮች ናቸው። በአርሲ፥ በአሰላና በሲሬ አባሎቻችን ስብሰባ ለማዘጋጀት ሲሞክሩ መከልከላቸው ብቻ ሳይሆን የስብሰባ ፈቃድ ለመጠየቅ የሄዱ የድርጅታችን አባላት በከንቲባዋ ቢሮ ግቢ ዉስጥ የኦሮሞ ብሄርተኛ ነን በሚሉ ወጣቶች ሲደበደቡ ከንቲባዋ እያዩ፤ ግቢው ውስጥ ያሉ የከተማው ፖሊስ አባላት ወንጀል ፈፃሚዎቹን ሲያበረታቷቸው ነበር። በዚያው ዞን በሌላ ወረዳ ስብሰባ ማድረግ የፈለጉ አባሎቻችን ስብሰብ ማድረግ ሲከለከሉ "ይህ እኮ ጠቅላይ ሚኒስትሩን ጨምሮ ሁላችንም የፖለቲካ ድርጅቶች በፈረምነው የጋራ ስምምነት የተፈቀደ ነው" ሲሏቸው ዐቢይ የፈለገውን ቢፈርም እኛን አይመለከተንም፤ ይልቅስ ሳትታሰሩ ከዚህ ጥፉ የተባሉበትን ሁኔታ ታዝበናል። በተመሳሳይ በደቡብ ክልል የወላይታ ዞን የቦዲቲ ከተማ ለፓርቲያችን ቢሮ ያከራዩ ሰዎችን በማስፈራራት ቢሮውን እንዲያስለቅቁ የማስጨነቅና ጥቃት እንደሚፈፅሙባቸው የሚያስፈራሩ ነበሩ፡፡

በአማራ ክልል ከላይ እንደጠቀስነው ብሄርተኛ ነን የሚሉ ወጣቶች ስብሰባ ሲበጠብጡ፤ ቢሮዎች ላይ የተለጠፉ ማስታወቂያዎችን ሲቀዱ፤ በባህር ዳር ውስጥ ደግሞ መሳሪያ ይዘው ስብሰባ ሲያውኩ የአካባቢው የፀጥታ ኃይሎችም ሆኑ የመስተዳድሩ መሪዎች እያዩ ዝም ያሉበት አንዳንዴም ተናበውና ተቀናጅተው ስብሰባዎቻችንን ያስተጓጎሉበትን ሁኔታዎች አይተናል። በኮንሶ የድርጅታችን አባላት የራሳቸውን የወረዳ ስብሰባ በቢሯቸው በሚያደርጉበት ጊዜ በዞኑ አስተዳዳሪዎችና በክልሉ የፀጥታ ኃይሎች ተባባሪነት ታስረዋል። በሳውላ፤ በቴፒ፤ በአርባ ምንጭና በሌሎች የደቡብ ክልል የሚገኙ አካባቢዎች አባሎቻችን ስብሰባ ለማድረግ ሲሞክሩ አዳራሽ ከመከልከል ጀምሮ ህዝቡን ለስብሰባ መቀስቀስ አትችሉም እየተባሉ በፖሊስ እስከመከልከል ደርሰዋል።

እነኝህ ሁሉ በደቡብ ክልል በየወረዳውና በየዞኑ የሚደረጉ የማሰናከል ሥራዎች የሚፈፀሙት የክልሉ መስተዳደር በጽሑፍ ማንኛውም በህግ የተመዘገበ የፖለቲካ ድርጅት ያለምንም እክል ስብሰባ ማድረግ እንዲችሉና ትብብርም እንዲደረግላቸው የሚጠይቅ ደብዳቤ ለሁሉም ዞኖች ካስተላለፈ በኋላ ነው። እዚህ ላይ በአንዳንድ አካባቢዎች ስብሰባ እንዳናደርግና ከህዝብ ጋር እንዳንገናኝ የተደራጁ የወጣት ስብስቦች እንቅፋት ሲፈጥሩብን ከክልልና ከፌዴራል ባለስልጣኞች ጋር በመነጋገር ችግሮችን መፍታት የቻልንበት ተደጋጋሚ ጊዜ እንዳለም እንዲታወቅ አፈልጋለሁ። ለዚህም ነው እነኝህ በታችኛው አካላት

የሚፈፀሙ እንቅስቃሴዎች ሁሉ በላይኛው የመንግሥት አካላት እውቅና የተደረጉ ናቸው ለማለት በርግጠኝነት የማንደፍረው። ይህ በአንድ በኩል የፌደራል መንግሥቱ የታችኛው እርከን ላይ ያሉ ኃላፊዎች የዜጎችን መብት እንዳይጥሱ ለመከላከል በአንዳንድ አካባቢዎች ላይ ያለውን የአቅም ውስንነት እንደዚሁም የቁርጠኝነት ማነስ ያሳያል፡፡ በአጠቃላይ ግን ይህ ምርጫ እውነትም የህዝብ ውክልና የሚገለጥበት እንዲሆን ከተፈለገ እነኝህን በየክልሉ በተለይም በታችኛው እርከን ላይ የሚገኙ የመንግሥት ጉልበተኞች በአስቸኳይ መቆጣጠር ካልተቻለ ይህ ምርጫ ከፍተኛ የተአማኒነት ችግር ውስጥ እንደሚገባ ግልጽ ነው።

## ሐ) በከፍተኛው የመንግሥት አካላትና በገዥው ፓርቲ እውቅና የሚፈጸሙ እክሎች፤

ዛሬ ኢትዮጵያ ውስጥ በመካሄድ ላይ የለውን ለውጥ ለማምጣት በተለያየ መስክ አስተዋፆ ካደረጉ ኃይሎች ውስጥ አሁን በስልጣን ላይ ያለው ገዢ ፓርቲ ውስጥ ያሉ አመራሮች አስተዋፆ ማድረጋቸው የሚያከራክር ጉዳይ አይደለም። ይህ በፊትም በገዢው ፓርቲ ውስጥ የነበረ ኃይል ወደ ሥልጣን እንደመጣ ለማህበረሰቡ የገባው ቃልኪዳን የአገሪቱን አንድነት አስጠብቆ ወደ እውነተኛ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት እንደሚያሸጋግረን ነው። ይህ ኃይል በታሪክ የተጣለበትን አደራ ይወጣል፤ ደግሞም ከተረጋጋና ከእውነተኛ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ውጭ ለአገራችን የሚያዋጣት ሌላ ምንም አማራጭ እንደሌለ ተገንዝቦ ይህንኑ ተግባራዊ ያደርጋል በሚል እምነት ነው አንዳንዶች እየቆረቆራቸውና እየተጠራጠሩም ቢሆን ለውጡን ተቀብለው በሒደቱ መሳተፍ የጀመሩት። በእንዲህ ዓይነት የሽግግር ጊዜ ሁሉ ነገር አልጋ በአልጋ ይሆናል ብሎ የጠበቀ ማንም አለነበረም።

ባለፈው አንድ ዓመት ተኩል የተፈጠሩ የተለያዩ ግጭቶችና ረብሻዎች በዚህ አሸጋጋሪ  ነው በሚባለው መንግስታዊ ቡድን የአቅም እና የቁርጠኝነት ማነስ ብቻ የተፈጠሩ ሳይሆኑ በአብዛኛው ለውጡን ለመቀልበስ በሚፈልጉ ሌሎች የፖለቲካ አደረጃጀቶችና ይህ መንግሥት ሙሉ ለሙሉ ሊቆጣጠራቸው ባልቻላቸውና ለውጡ ከተቀመጥንበት የሥልጣን ማማ ያወርደናል ብለው በሚያምኑ የክልልና የታችኛው እርከን የመንግሥት ባለስልጣናት እንደሆኑ የምንገነዘበው ጉዳይ ይመስለኛል። የለውጥ ኃይል ነው የሚባለው አዲስ በመሰረተው በ "ብልጽግና ፓርቲ" በኩል የሽግግር ኃላፊነቱን "በአዲስ መንፈስና ፍልስፍና" ከትግራይ ክልል ውጭ ያሉትን ሁሉንም የክልልና ከዚያ በታች ያሉትን መስተዳደሮች በብልጽግና ፓርቲ ስር ማስገባቱ የሚታወስ ነው። ይህ ከሆነ በኋላ በየክልሉ የሚደረጉ የአስተዳደር በደሎችና የአድሎ አሠራሮች (ሙስና)፤ የዴሞክራሲያዊ ሂደቱን በተለይም የምርጫውን ተአማኒነት የሚያሳጡና ሀሳቦች በነጻነትና በሰላም እንዳይንሸራሸሩ የሚያሰናክሉ ተግባራት፤ ወይም ምርጫው በፍትሃዊነት እንዳይካሄድና ወደ ገዥው ፓርቲ እንዲያደላ በአደራ የወሰደውን የመንግሥት ኃብትና መዋቅርን እራሱን ለማስመረጥ በሚል በየትኛውም መልክ ከተጠቀመበትና ምርጫው ተአማኒነት ካጣ፤ በሽግግሩ ሂደቶች ለሠራቸው ጥሩ ሥራዎች የምናመሰግነውን ያህል ዋናውን የመዳረሻ ሂደት ካበላሸው የለውጥ ኃይሉን በግልጽ ከመኮነንና ተጠያቂ ከማድረግ በፍጹም ወደኋላ እንልም!

ይህ ደግሞ እስካሁን የተደረገውን ጥረት ሁሉ ጥላሸት የሚቀባ ነው። ይህን የምንለው ዝም ብለን በግምት አይደለም። እንዲህ ዓይነት ፍርሀቶች የሚቀሰቅሱ የተለያዩ ተግባራት በተጨባጭ እያየን ስለሆነ ነው።  የቀድሞው ሥርዓት በማህበረሰባችን ላይ ካመጣው ትላልቅ ችግሮች ውስጥ አንዱ በተቀነባበረ መንገድ በመንግሥት ባለሥልጣኖችና ከነሱ ጋር በተሞዳሞዱ ባለሀብቶች ይደረግ የነበረው አይን ያወጣ ዝርፊያ ነበር። ይህን ያዩ የታችኛው የመንግሥት ባለሥልጣኖችም  እንደአቅማቸው በየአካባቢው "ይገባናል ብለው ያሰቡትን" እየዘረፉ ኖረዋል። ዜጎች መሰረታዊ መብታቸው ስለሆነ ያለውጣ ውረድ ማግኘት

የሚገባቸውን አገልግሎቶች ለምሳሌ መታወቂያ ማውጣት፥ የሀብት ሽያጭና የውህና መብራት ማግኘትን የመሳሰሉ የመንግሥት አገልግሎቶች መደለያ እየከፈሉ የሚያገኙበት ሁኔታ ተፈጥሯል። የዚህ ዓይነት የሙስና አሠራር አሁንም በከፍተኛ ደረጃ እንዲያውም አንዳንዶች እንደሚሉት በከፋ ሁኔታ እንደቀጠለ ነው። ይህን ሁኔታ ለማጽዳት ጊዜ የሚወስድና የማህበረሰቡን ሙሉ ተሳትፎ የሚጠይቅ ቢሆንም፤ ችግሩ የሚቀንስበት ሁኔታ በቶሎ ካልታየ ካሁን በኋላ ማህበረሰቡ ኃላፊነቱን ከገዥው ፓርቲ ጋር ማያያዙ የማይቀር ነው። በተለይ ከምርጫው ጋር በተያያዘ ለገዢው ፓርቲ ማስመረጫ ገንዘብ ማሰባሰብ በሚል እየተሄደበት ያለው መንገድ የምርጫውን የመወዳደሪያ ሜዳ እጅጉን ሚዛናዊነት (Fairness) የጎደለው እንዲሆን ከማድረጉም በላይ ከምርጫው በኋላ ሊመጣ የሚችለውን የሙስና አካሄድ የሚያሳይ ነውና ካሁኑ ጥንቃቄ ሊደረግበት ይገባል። በዚህ ሂደት የመንግሥትና የፓርቲ ኃላፊነቶችን የሚያደበላልቁ እርምጃዎች ማየታችን እጅግ አሳሳቢ ነው። የፓርቲ ሳይሆን የመንግሥት ኃላፊነት ያለባቸው የገቢዎች ባለስልጣን ኃላፊዎች የሚቆጣጠሩትን የንግድ ማህበረሰብ ለብልጽግና ፓርቲ ገንዘብ እንዲያወጣ ሲጠይቁ፤ ባንዳንድ ቦታ (ለምሳሌ በአዳማ ከተማ ባንድ ክፍለ ከተማ) የገቢዎች ባለስልጣን ማህተም ባለበት ደብዳቤ ነጋዴዎች ለብልጽግና ፓርቲ ገንዘብ እንዲያስገቡ ሲጠየቁ እነኝህ ነጋዴዎች ለሚደግፉት ፓርቲ በፈቃደኝነት ገንዘብ ሰጥተናል ብለው ሳይሆን ካልከፈልን ነገ ያላግባብ ግብር ይጫንብናል ብለው ፈርተው እንደሚሆን አለማሰብ እንዲፈጠር እንፈልጋለን የሚሉትን ሥርዓት ምንነት በቅጡ አለመረዳት ነው። በተለይም አንዳንዶቹን የከተማው የወረዳ ኃላፊዎች ገንዘቡን ባንክ ካላስገባችሁ ሱቃችሁን እናሽጋለን በማለት እስከማስፈራራት ድረስ የደረሱም አሉ፡፡ በተጨማሪም በአክስዮን የተቋቋሙ ድርጅቶችን ለምሳሌ ባንኮችና ኢንሹራንሶች (በሺዎች የሚቆጠሩ ባለአክሲዮኖች ያሏቸው እንደመሆኑ) እንደ ተቋም አንድን ፓርቲ እንዲደግፉና የተመደበ መዋጮ እንዲያደርጉ በፓርቲው ስምና እነኝህን ተቋሞች በሚቆጣጠሩ የመንግሥት አካላት ገፋፊነት ሲጠየቁ፤ ባለአክሲዮኖቹ የተለያዩ ድርጅቶችን ሊደግፉ እንደሚችሉ፤ የነሱን ገንዘብ ደግሞ ተቋሞቹ ለአንድ ድርጅት ገንዘብ ማዋጣት እንደማይገባቸው፤ ግን ሲያዋጡም ፈርተው እንጂ አምነውበት እንደማይሆን ባንኮችና ኢንሹራንሶች አካባቢ ካሉ ኃላፊዎች "ይህ ነገር እንዴት ነው? ካለፈው አልተቀየረም እንዴ?" የሚል ፍርሀት እንደገባቸው እየሰማን ነው። እነዚህ ግምቶች አይደሉም በተጨባጭ መረጃዎች ያገኘናቸው ናቸው። የዚህ አካሄድ አስፈሪነት ይህን የሚያደርጉት የመንግሥት ባለሚሎች ይህ ድርጊት "ስህተት መሆኑን" እንኳን የሚረዱ አለመሆናቸው ነው። የብልጽግና ፓርቲ እንደ ፓርቲ ተነጋግሮና አምኖበት ሳይሆን በውስጡ ያሉ አንዳንድ "የቀድሞው አሠራር አባዜ" ያልለቀቃቸው አባላቱ ከሆነ ይህን የሚያደርጉት፤ ቢያንስ አባላቱን ማሠልጠን፤ በመንግሥትና በፓርቲ መሀከል ያለውን ቀይ መስመር እንዳይሻገሩ ማስተማር ከዚያም በላይ እንዲህ ዓይነት ሥራ የሚሠሩ አባሎቹ ላይ የማያዳግም እርምጃ መውሰድ ይጠበቅበታል። አለበለዚያ የምርጫውን አካሄድ ክፉኛ ሊያበላሸውና ወደምንፈራው ሥርዓት አልበኝነት ወይንም አዲስ ዓይነት አምባገነናዊ ሥርዓት ሊወስደን ይችላል። ይህ የሽግግር ሂደት ደግሞ የለውጥ ኃይል እየተባለ ሲሞካሽ በነበረው ኃይል አጋዥነት ከተቀለበሰ የበለጠ አሳፋሪና አስፈሪ አደጋ አገራችን መውሰዱ አይቀሬ ነው። ምርጫውን ነጻና ፍትሃዊ (Free & Fair) የማድረግ ኃላፊነት ያለበት ምርጫ ቦርድም እንዲህ ዓይነት የምርጫውን ፍትሃዊነትና ዴሞክራሲያዊ ሂደት የሚያዛቡ ኹነቶችን በጥንቃቄ መመልከትና ማስተካከያ እርምጃዎችን በፍጥነት መውሰድ ካልቻለ/ካልፈለገ እሱም ይህ ትልቅ አገራዊ ፕሮጀክት እንዲሳካ ግዴታውን ባለመወጣት በኢትዮጵያ ሕዝብም በታሪክም ትዝብት ውስጥ መውደቁ አይቀርም።

***ውድ ኢትዮጵያውያን ወገኖቼ!!!!***

ይህ መልዕክቴ በመግቢያዬ ላይ እንዳልኩት ከፊታችን ያለው ምርጫም ሆነ በምርጫው በኩል እንደ አገር ልንጀምር የምናስብው ዴሞክራሲያዊ ሥርዓትና ሕዝባዊ መንግሥት በቀላሉ የሚገኝ እንዳልሆነ ነው። በዚህ መልዕክት የጠቃቀስኳቸው እንቅፋት ሊፈጥሩ ይችላሉ ያልኳቸው አካላት ብቻ አይደሉም አዲስ ዴሞክራሲያዊ ባሕል የመፍጠር ጥረታችን ላይ እንቅፋት የሚሆኑብን። የተለያዩ ትላልቅና ትናንሽ ችግሮችን እየፈጠሩ የአዲስ ሥርአት ግንባታ ጥረታችንን በቀጥታ ከሚያሰናክሉ ኃይሎች ባልተናነሰ መንገድ እነዚህ ችግሮች ሲፈጠሩ "ምን አገባኝ" ብሎ በዝምታ የሚመለከተው የህብረተሰብ ክፍልም (the silent majority) በቀጥታም ባይሆን በተዘዋዋሪ አስተዋፆ ያደርጋል። ለዚያ ነው ይህ የህብረተሰብ ክፍል ማድረግ የሚችለውን ነገር ዝምታን መርጦ ሳያደርግ ቢቀር በኋላላይ ለሚመጣው ነገር የድርሻውን ኃላፊነት የሚወስድ መሆኑን አውቆ ከወዲሁ ዝምታውን ሰብሮ የአገሩ ጉዳይ ላይ በንቃት መሳተፍ፤ ትውልድና ታሪክ የሚጠይቀውን ኃላፊነት መወጣት እንዳለበት ማስገንዘብ የምፈልገው፡፡

የዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ግንባታ የመንግሥት ኃላፊነት ብቻ ሳይሆን የእያንዳንዱን ኢትዮጵያዊ አስተዋፆ ይጠይቃል። ስለዚህም ነው ይህ ጥሪ ለሁሉም የሀገራችን ማህበረሰብ የሆነው።

***ውድ ወጣት ወገኖቼ ሆይ!***

ከማንም በላይ የዴሞክራሲያዊ ሥርዓት መፈጠር በረጅሙ ጊዜ የሚጠቅመው እናንተን ነው። እኛ በወጣትነታችን ያደረግነውን ስህተት እንዳትደግሙ መጠንቀቅ አለባችሁ። በጊዜው በስሜት ተነድተን፤ በደንብ ያላላመጥነውን ርዕዮተ አለም እንደ ሃይማኖት ይዘን፤ የተገራ የመንግሥት ሥርዓት ለማቆም ሳይሆን ስሜታችንን በተቆጣጠረው የጊዜው ርዕዮተ አለም ተነድተን አገራችንን እስካሁን ልትወጣበት ወዳልቻለችው መከራ ዳርገናታል። በዚህ ሂደት ከማንኛውም የህብረተሰብ ክፍል ይልቅ እኛ ተጎዳን። ወጣት ወንድም እህቶቻችንን፤ የቅርብ ዘመዶቻችንንና ጓደኞቻችንን ገብረን አገሪቱን ለከፋ አምባገነናዊ ሥርዓት ዳረግናት። እናንተም አሁን የገጠማችሁን የህይወት ችግሮችና ከዚህም የመጣውን ብስጭታችሁን እየቆሰቆሱ የአጭር ጊዜ ችግራችሁ ላይ አተኩራችሁ ዘላቂውን የአገራችንና የራሳችሁን ጥቅም እንዳታዩ ለሚጋርዱ̃ችሁ ኃይሎች መሳሪያ አትሆኑ! እውነተኛ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ሲፈጠርና ማህበረሰቡ የሚቆጣጠረው መንግሥት ሲመሰረትና ሁላችንንም በእኩልነት የምታስተናግድ አገር ስትኖረን ብቻ ነው የናንተም የሁላችንም ኢትዮጵያውያን መሰረታዊ ችግሮች ዘላቂ መግትሄ ማግኘት የሚችሉት!

***የሀገራችን ምሁራን ሆይ!***

ይህ የለውጥ ሂደት ይዞልን የመጣውን እድል በድጋሚ እንዳናጣው ከፍተኛ ሚና መጫወት ይጠበቅባችኋል። ለምሁራን ከማንኛውም በላይ አስፈላጊ የሆነው ነገር በነጻነት ማሰብና መናገር መቻል ነው። በዚህ ሂደት ላይ ይህንን በዘላቂነት እንዳናገኝ እንቅፋት የሚሆኑ ኃይሎችን መገሰጽ፤ የአካሄዳቸውን ስህተት ማሳየት፤ በማስፈራራት አንገታችሁን እንደቀድሞው ለማስደፋት የሚፈልጉ ኃይሎችን በዝምታ ማለፍ ሳይሆን በግላጭ ማጋለጥ የምሁርነታችሁም ሆነ የዜግነት ኃላፊነታችሁ መሆኑን አውቃችሁ በንቃት የምትሳተፉበትና በታሪክ ሚዛን ውስጥ ለትዝብት የምትወድቁበት ወሳኝ ጊዜው አሁን ነው!

በአድርባይነት ማድረግ የሚገባችሁን ሳታደርጉ ብትቀሩ፤ ወይንም ለጊዜያዊ ጥቅም ብላችሁ ማድረግ የሌለባችሁን ብታደርጉ በታሪክ ፊት ትዝብት ውስጥ የምትወድቁ መሆኑን እወቁት!

## የተከበራችሁ የአገራችን የንግዱ ማህበረሰብ አባላት!

ይህ የለውጥ ሂደት በትክክል ከሄደ እውነትም በዕጅግ ተጠቃሚ ትሆናላችሁ። የንግድ ልውውጥን በአድሎ ወይም በሙስና ሳይሆን ለሁሉም እኩል በሆነ መጫወቻ ሜዳ፤ በየትኛውም የሀገሪቱ ክፍል የምትወዳደሩበት፤ በዚህም ሂደት ራሳችሁንም ሆነ አገራችሁን የምትጠቅሙበት እድል ነው ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ይዞላችሁ የሚመጣው። ይህን እድል "ነገ ስልጣን ላይ የሚወጣውን" ኃይል እየተነበዩ ያንን ኃይል እንዴት ተጠግተው ለነገው በሙስና እንዴት እንደሚበለጽጉ የሚያስቡ በውስጣችሁ ያሉ አድርባዮችን ከመከተል ይልቅ በእኩልነት የዜግነት መብታችሁ ተጠብቆ የምትሰሩበት ሁኔታ እንዲፈጠር ጫወታውን ለማበላሸት ለሚሞክሩ ኃይሎች ሰለባ እንዳትሆኑ ተጠንቀቁ!

## የተከበራችሁ የፀጥታ ኃይል አባላት፣

ሕግ ማስከበር ሕገ-መንግስታዊ ግዴታችሁ ቢሆንም፤ ሙያዊ ክብር የሚያጎናፅፋችሁና በህዝብ ዘንድ አመኔታንና ሞገስን የሚያላብስ ኃላፊነታችሁ ነው፡፡ ህጋዊ ስብሰባዎች በነውጠኞች ሲስተጓጎሉና የህዝብ የተለያዩ አማራጭ ሀሳቦችን የመስማት መብቱ ሲጣስ ከዚህም አልፎ በሰላም የመኖር ሕገ-መንግስታዊ መብት ሲጣስ እያያችሁ ዝም ማለት በህግም በሞራልም ያስጠይቃል፡፡ የለበሳችሁትን መለዮና የተሸከማችሁትን የህዝብ አደራ ወደጎን በማለት መንግሥታዊም ሆኑ መንግሥታዊ ላልሆኑ ኃይሎች ሙያዊ ግዴታችሁን አለመወጣት ከባድ ሀገራዊ ቀውስ ውስጥ ሊከተን ይችላል፡፡ ሕዝቡ እናንተ ላይ ያለው እምነት ከጠፋ እና የአንድ የፖለቲካ አመለካከት ወይንም የዘውግ ማኅበረሰብ ብቻ ጠባቂ አድርጎ ማየት ከጀመረ የሚፈጠረው የፍርሃት መንፈስ ወደማንወጣው ቀውስ ይዞን ይሄዳል፡፡ ይህ ከኃላፊነታችሁ አንጻር ብቻ ሳይሆን እንደዜጋም ሊያሳስባችሁ ይገባል፡፡

## የቃልኪዳን ስምምነት ለፈጸማችሁ የፖለቲካ ድርጅቶች፣

በፈረምነው የቃል ኪዳን ሰነድ መሰረት እንድንንቀሳቀስ እና በህብረትና በአንድነት ለአገርና ለህዝብ እንድንሠራ፤ በጉስቁልናና በድህነት ለሚማቅቀው ህዝብ የተሻለ አማራጭ ሃሳብ ለማቅረብ እንድንዘጋጅ፤ ከዚህ ውጪ የህዝብን ሰላምና አንድነት እንዲሁም መረጋጋት ለማረጋገጥ የምንችለውን ሁሉ በቅንነት እንድናደርግ፣ ይህን ሳናደርግ ብንቀር ከታሪክ ተጠያቂነት አለማምለጥ ብቻ ሳይሆን፣ የራሳችንንም ደህንነት ችግር ውስጥ የምንጥል መሆናችንን ተገንዝበን፣ በተረጋጋ ሁኔታ ያለብንን ኃላፊነት እንድንወጣ አደራ እላለሁ።

## በውጭ የምትኖሩ ኢትዮጵያውያን እና ትውልደ ኢዮጵያዊያን!

ይህ ለውጥ እንዲመጣ ብዙ ታግላችኋል። ከለውጡ በኋላ በየቦታው የተፈጠሩ አክራሪ ኃይሎች ለውጡን ለማደናቀፍ ለሚወስዷቸው እርምጃዎች ዱላ አታቀብሉ። ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ውስጥ መብታችሁና ነጻነታችሁ እየተከበረላችሁ

እየኖራችሁ ለትውልድ አገራችሁ ቢያንስ እናንተ ያገኛችሁትን ትመኛላችሁ ተብሎ ይታሰባል። ቢያንስ አገሪቱን ለማተራመስና የተጀመረው ለውጥ ግቡን መቶ አገራችን ለዘመናት ስትናፍቀው የነበረውን ዴሞክራሲያዊ ስርአት እንዳትጀምር የሚደረገውን ባብዛኛው በውሸት ላይ የተመሰረተ የፕሮፓጋንዳ ዘመቻ ማስቆም እንኳን ባትችሉ፤ ያንን የሚያበረታታ እንቅስቃሴ ከማድረግ ተቆጠቡ። ለእረፍትም ሆነ ወደፊት አገሬ ብላችሁ የምትኖሩበት ቦታ አሁን እንዳላችሁባቸው አገሮች የዜጎች መብት የተከበረበት፤ ከአድሎ የጸዳ የመንግሥት ሥርዓት የሚኖርበት እንዲሆን ማገዝ እዚህ ላሉት ዘመዶቻችሁ ብቻ ሳይሆን ለራሳችሁም ይበጃል!!

## በየትኛውም ክልል የምትገኙ ውድ ኢትዮጵያዊ ወገኖቼ!

ለአገራችሁ ሰላምና ልማት የምታስቡና በገዛ አገራችሁ ጉልበተኞችን እየፈራችሁ፤ ነጻነታችሁን ተነፍጋችሁ፤ “ፖለቲካን በሩቁ” ብላችሁ ዝም ብላችሁ የምታዩ ወገኖች! ይህ አሁን ያለንበት ጊዜና የተጀመረው የለውጥ ሂደት ከተቀለበሰ ዝም ስላላችሁ የሚተዋችሁ ወይንም የሚያልፋችሁ ፍዳ አይኖርም። ለውጡ ተደናቅፎ ሥርዓት አልበኝነት ከነገሰ ወይንም ሌላ አዲስ ዓይነት አምባገነናዊ ሥርዓት ዳግም ከተፈጠረ፤ አንገታችሁን አቀርቅራችሁ በሰላም የምትኖሩበት አገር እንኳን አይኖራችሁም። ከማንኛውም ድርጅት ማሸነፍ በላይ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓቱ በሁለት እግሩ መቆሙ ነው የሰላማችሁም ሆነ የነጻነታችሁ መከታ፣ ካሁኑ ለዚህ ሥርዓት ምስረታ አስፈላጊ የሆነው የጨወታ ሕግ በማንም ጉልበተኛ ሲደናቀፍ ዝም ብላችሁ ለማየት አይቻላችሁም። ለአንድ ድርጅት ሳይሆን ለሥርዓቱ መመስረት ዘብ ቁሙ!!

## በመጨረሻም ይህንን የሽግግር ሂደት ከዳር እንዲያደርስ አደራ ላለበት መንግሥት አጭር መልእክት አስተላልፌ ላብቃ።

ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት እንመሰርታለን ብላችሁ ቃል ገብታችኋል። ይህ ሂደት ከተሰናከለ መጪው ያገራችን እጣ ፈንታ አስከፊ እንደሚሆን ከናንተ በላይ የሚያውቅ የለም። ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ከምንም በላይ ሂደት ነው። ይህን ሂደት የሚያበላሹ ማናቸውንም ኃይሎች የመቆጣጠርና ኃርዓት የማስያዝ ሀላፊነቱም ሆነ ቢጋራ እንደ ህዝብ የሰጠናችሁ ትልቅ አቅም ያለው እናንተ ጋር ነው፡፡ እናንተ ይህን መቆጣጠር ብቻ ሳይሆን በውስጣችሁ ያሉ ይህን ሂደት የሚያበላሹ ኃይሎችን የመግራት ትልቅ ኃላፊነትና ግዴታ አለባችሁ። ይህን ህዝባዊ አደራ በብልህትና በቆራጥነት ትወጣላችሁ ብለን እንጠብቃለን።

### ፈጣሪ አገራችንን ይባርክ !!!

### ስላዳመጣችሁኝ ከልብ አመሰግናለሁ።